የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ግንኙነት ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ስነፅሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# በአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ

## (በጉራጌ ዞን በመስቃን ወረዳ በ8ኛ ክፍል በተመረጡ አራት የመጀመሪያ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)

በ አይናለም ጴጥሮስ

ጥቅምት 2016 ዓ.ም.
አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ

**በጉራጌ ዞን በመስቃን ወረዳ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ (በተመረጡ አራት የመጀመሪያ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)**

**በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር**

**ለ በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም-ኤ-ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት**

**አማካሪ**

**ታደሰ ሲባሞ(ዶ/ር)**

በጉራጌ ዞን በመስቃን ወረዳ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ትንተና (በተመረጡ አራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት); በሚል ርዕስ የተሰራው ይህ ጥናት የራሴ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም አይናለም ጴጥሮስ

ፊርማ --------------------------

ቀን ጥቅምት 2016 ዓ.ም.

**በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒዩኬሽን፣ የአማርኛ ቋንቋ**

**ስነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር**

**ለ በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም-ኤ-ዲግሪ**

**ማሟያ የቀረበ ጥናት**

**የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ**

**አማካሪ**

**ዶ/ር ታደሰ ሲባሞ**

---------------------------------------- ------------------------------------

**ፈታኝ** **ፊርማ**

**ዶ/ር ዳዊት ፍሬህይወት**

-------------------------------------- ------------------------------------

**ፈታኝ ዶ /ር በኀሰው የሺዋስ** **ፊርማ**

--------------------------------

## ምስጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ በድካሜ ብርታትና አቅም ለሆነኝ ለልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይግባው። በመቀጠል ጥናቴ የተሳካ እንዲሆን በመከታተልና አቅጣጫ በማስያዝ እንዲሁም ስራዬን የዘነጋው ሲመስለኝ በማስታወስ ላበረታቱኝና አባታዊ የሆነ ምክራቸውን በመለገስ ለረዱኝ ውድ መምህሬና አማካሪዬ ለዶ/ር ታደሰ ሲባሞ ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። እንዲሁም ከጎኔ ሆነው ላበረታቱኝ ሞራላዊ ድጋፋቸውን ለሰጡኝና ወደ ትምህርት ሄጄ እስክመለስ ልጆቼን በመጠበቅ እና በመንከባከብ ለረዱኝ ለውድ ቤተሰቦቼ ለእህቴ ለካሰች ጴጥሮስና ለባለቤቷ ምትኩ ባልቻ ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በመቀጠል ጥናቱን ለማካሄድ መረጃ ለሰጡኝ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በሙሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።በተጨማሪም ይህንን የትምህርት እድል የሰጠኝን የመስቃን ወረዳ ትምህርት ቢሮና ወጪውን በመሸፈን ለተባበረኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ከልብ አመሰግናለሁ።

# አጠቃሎ


*የዚህ ጥናት ዋና አላማ በጉራጌ ዞን በመስቃን ወረዳ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርን መፈተሸሽ ነው። ይህንንም አላማ ከግብ ለማድረስ ገላጭ የምርምር ዘዴን ተግባራዊ ተደርጓል። ለዚህም ጥናቱ በሚያካትታቸው አራት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ፈትሹአል። በጥናቱ መስቃን ወረዳንና በውስጡ በሚገኙ የተመረጡ የ8ኛ ክፍልን በአመቺ ናሙና የተመረጡ ሲሆን በጥናቱ የተካተቱትም ትምህርት ቤቶች በቀላል የእጣ ናሙና የተመረጡ ናቸው። በተመረጡበት ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል ከሚያስተምሩ መምህራን በየትምህርት ቤቱ አንድ አንድ በድምሩ አራት ሲሆኑ፣ በጠቅላይ ናሙና ተወስደው በጥናቱ ተካተዋል። እንዲሁም ከተመረጡ ትምህርት ቤቶች አንድ አንድ ምድብ በቀላል የአእጣ ናሙና በመውሰድ ከየምድቦቹ ከሚገኙ ተማሪዎች መካከል ከግማሽ በታች ያህሉ በጥናቱ ለማካተት ሲባል በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ከየምድቡ 20 በድምሩ 80 ተማሪዎች በጥናቱ ተካተዋል። ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችም በተደጋጋሚ በተካሄደ የክፍል ውስጥ ምልከታና በመምህራንና በተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ መሰረት መረጃውን ለመሰብሰብ ተችሏል። ከእነዚህም መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የተገኙትን ምላሾች በቁጥርና በመቶኛ በማስቀመጥ በገለፃ/ በአይነታዊ /መተንተኛ ዘዴ ተተንትኖ ቀርቧል። በዚህም መሰረት በመምህራንና በማዳመጥ ክሂል አተገባበር መካከል የሚታዩትን በርካታ ክፍተቶችና ጉድለቶች በራሳቸው በመምህራኑ ሊሻሻሉ የሚገቡ ጉዳዮች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል። መምህራን ከላይ የሚታዩባቸውን ችግሮችና ክፍተቶች ለመመልከት ራሳቸውን በተለያዩ ስልጠናዎች በየደረጃ የንባብ ክህሎታቸውን ቢያሻሽሉና በተለያዩ ልምድ ልውውጦችን ቢያደርጉ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት አተገባበር የተዋጣለት ሊሆን እንደሚችል ጥናቱ ይጠቁማል።*

## ማውጫ


ምስጋና ............ i

አጠቃሎ ............ ii

የሰንጠረዥ ማውጫ ............ v

ምዕራፍ አንድ ............ 1

መግቢያ ............ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ............ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............ 2

1.3 የጥናቱ አላማ ............ 2

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ............ 3

1.5 የጥናቱ ወሰን ............ 3

ምዕራፍ ሁለት ............ 4

ክለሳ ድርሳናት ............ 4

2.1. የማዳመጥ ክሂል ምንነት ............ 4

2.2. የማዳመጥ ትምህርት ምንነት ............ 4

2.2..1. የማዳመጥ ትምህርት አላማ ............ 5

2.3 የማዳመጥ ትምህርት ክንዉኖች የአተገባበር ደረጃዎች ............ 6

2.3.1 ቅድመ ማዳመጥ (pre-listening) ............ 6

2.3.2 የማዳመጥ ጊዜ ተግባር (while listening) ............ 6

2.3.3.ድህረ ማዳመጥ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ............ 7

2.4 በማዳመጥ ትምህርት ወቅት የመምህሩና የተማሪው ተግባር ............ 7

2.4.1 በማዳመጥ ትምህርት ወቅት የመምህራን ተግባር ............ 7

2.4.2. ከትምህርት በፊት የሚከናወኑ የመምህሩ ተግባራት ............ 8

2.4.3. በማዳመጥ ትምህርት ወቅት የተማሪዎች ተገባር ............ 8

2.5 የማዳመጥ ክሂልን ውጤታማነት የሚያሰናክሉ ጉዳዮችና መፍትሔዎቻቸው ............ 9

2.5.1 መፍትሔዎቻቸው ............ 9

2.6 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ............ 10

ምዕራፍ ሶስት ............ 13

የአጠናን ዘዴ ............ 13

3.1መረጃ ምንጮች ............ 13

3.2 የናሙና አወሳሰድ ........ 13
3.2.1 የትምህርት ቤቶች የናሙና አወሳሰድ ........ 13
3.2.2 የክፍል ደረጃ አመዳደብ ........ 13
3.2.3 የምድብና የተማሪዎች ናሙና ........ 14
3.2.4 የመምህራን አመራረጥ ........ 14
3.3 የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 14
3.3.1.ምልከታ ........ 15
3.3.2.የፅሁፍ መጠይቅ ........ 15
3.4 የመረጃ ትንተና ........ 16
ምዕራፍ አራት ........ 17
የመረጃ ትንተና ........ 17
4.1. የተጠኚ መምህራንና ተማሪዎች ዳራ ........ 17
4.1.1. የተጠኚ መምህራን ዳራ ........ 17
4.1.2 የተጠኚ ተማሪዎች ዳራ ነክ ጉዳዮች መግለጫ ........ 19
4.2 በ2015 ዓ/ም ሥራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ መልመጃዎች ብዛት ........ 20
4.3 መምህራንና ተማሪዎች ስለማዳመጥ ክሂል ትምህርት ያላቸው አመለካከት ........ 21
4.3.1 መምህራን ስለማዳመጥ ክሂል ያላቸው አመለካከት ........ 21
4.3.2 የተማሪዎች ስለማዳመጥ ክሂል ትምህርት ያላቸው አመለካከት ........ 22
4.4 የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ ተግባራት አፈፃፀም ........ 22
4.4.1 የቅድመ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም ........ 23
4.4.2 የማዳመጥ ጊዜ ክንውን አፈፃፀም ........ 27
4.4.3 የድህረ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም ........ 31
4.5 በማዳመጥ ትምህርት ወቅት ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች እና መፍትሔዎቻቸው፡- ........ 35
ምዕራፍ አምስት ........ 37
የማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳቦች ........ 37
5.1 ማጠቃለያ ........ 37
5.2 የመፍትሔ ሀሳቦች ........ 38

# የሰንጠረዥ ማውጫ


ሰንጠረዥ 1 ፡- የመምህራንን ዳራዊ ሁኔታ የሚያሳይ ........ 18
ሰንጠረዥ 2፡- የተማሪዎች ዳራዊ ሁኔታ የሚያሳዩ ........ 19
ሰንጠረዥ 3 ፡- በ2015 ዓ/ም ስራ ላይ የዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃፍት ውስጥ የሚገኙ መልመጃዎች ብዛትና የይዘት ክፍሎች የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........ 20
ሰንጠረዥ 4 ፡- መምህራን ስለማዳመጥ ክሂል ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምላሽ ፍተሻ ........ 21
ሰንጠረዥ 5፡- ተማሪዎች ስለማዳመጥ ክሂል ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምላሽ ፍተሻ ........ 22
ሰንጠረዥ 6፡- ስለቅድመ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም ከክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘ ምላሽ ትንታኔ 23
ሰንጠረዥ 7 ፡- ስለ ቅድመ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም ከመምህራን የፅሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽና ፍተሻ ........ 24
ሰንጠረዥ 8 ፡- ስለቅድመ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ፍተሻ ........ 25
ሰንጠረዥ 9፡- ስለማዳመጥ ጊዜ ክንውን አፈፃፀም ከክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘ ምላሽ ፍተሻ ........ 28
ሰንጠረዥ 10 ፡- ስለማዳመጥ ጊዜ ክንውን ከመምህራን የፅሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ፍተሻ ........ 29
ሰንጠረዥ 11 ፡- ስለ ማዳመጥ ጊዜ ክንውን አፈፃፀም ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ፍተሻ ........ 30
ሰንጠረዥ 12፡- ስለ ድህረ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም ከክፍል ምልከታ የተገኘ ምላሽ ፍተሻ ........ 32
ሰንጠረዥ 13 ፡- ስለ ድህረ ማዳመጥ ክንውን ከመምህራን የፅሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ፍተሻ ... 33
ሰንጠረዥ 14 ፡- ስለ ድህረ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ፍተሻ ........ 34

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ማዳመጥ ከሌሎች ክሂሎች ቀዳሚው ነው። ይህንም ቀዳሚ ክሂል በተመለከተ ማረው (1998፡123) ‹‹ ማዳመጥ ከሌላ የተነገረውን ወይም የተነበበውን የመገንዘብ ወይም የመረዳት ክንዋኔ ነው›› በማለት ይገልጻሉ።

ማዳመጥ በሰው ልጅ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ትልቁን ሚና ይጫወታል። ይህን አስመልክተው Celce-murcia (1991-82) "ማዳመጥ በሰው ልጆች የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ውስጥ ከሚኖረው ሚና አንጻር ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። በመሆኑም ከምንናገረው እጥፍ እንድናዳምጥ ይጠበቃል"ሲሉ ፍቅሩ (2002፡2) ዳግም Moctcheonet.al (1994) ን በዋቢነት ገልፀዋል።

አንድ በማዕከላዊ የእድሜ ደረጃ የሚገኝ ሰው በተግባቦት ሂደት 45%በማዳመጥ 30 % በመናገር 16 % በማንበብ 9 % በመጻፍ ጊዜውን ያሳልፋል። ስለዚህ የማዳመጥ ክሂል ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም በማለት ይገልጻሉ። የማዳመጥ ትምህርተን በተመለከተ Kral (1996:32) እንደገለጹት በበርካታ ሀገሮች አዳምጦ መረዳት የተማሪዎች ችግር መሆኑ ይታመናል::ምሁሩ አክለውም ሲናገሩ፣ ለዚህም ነው የማዳመጥ ትምህርት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው:: ምክንያቱም የማዳመጥ ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎች ጥሩ አዳማጭ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። በመሆኑም ህጻናት ከቤተሰቦቻቸውና ከአካባቢያቸው ይዘውት የመጡት ተፈጥሮአዊና ተለምዷዊ በሆነ መንገድ የሚደረግ ተራቢቻውን ማጎልበት ጥሩ አድማጭ ለመሆን አያበቃም። ጥሩ አድማጭ ለመሆን ማዳመጥና የመማር መንገድ በትምህርት መታገዝ አለበት በማለት ገልጸዋል:: Underwood(1989:4) በበኩላቸው፤

> የማዳመጥ ትምህርት አላማ ተማሪዎችን ማዳመጥን በማስተማር ጥሩ አድማጭ በማድረግ በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ በመልካም ሁኔታ የመግባባት ብቃት እንዲኖራቸው ማድረግ እንዲሁም ክሂሉን በማዳበር ያደመጡትን እንዲገነዘቡ፣ የተገነዘቡትንም በተግባር እንዲያሳዩና ካደመጡት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ምላሽ እንዲሰጡ ማለማመድ ነው በማለት

ይገልጹታል፡፡ Grant (1987:19) የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት እንዲያሳድግና ትምህርታቸውንም በቀላሉ እንዲከታተሉ እንዲሚያደርግ ይገልጻሉ፡፡ እንዲሁም Byrne (1986:15) ደግሞ የማዳመጥን ክሂል የማስተማር አላማ ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚሰጡትን ቋንቋ የበለጠ እንዲያዳብሩት ለማድረግ፣ ተማሪዎች ከንግግሩ አውድ መልዕክት የመረዳት ችሎታቸውን እንዲዳብርና ማዳመጥን እንደመነሻ በማድረግ ሌሎች ተግባራትን እንዲያከናውኑ ለማስቻል ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የዳበረ የመዳመጥ ችሎታ እንዲኖራቸውና በሌሎች የቋንቋ ክሂሎችና ትምህርቶች አመርቂ ውጤት እንዲያመጡ ለማስቻል የማዳመጥ ትምህርት በተገቢው መንገድ ሊሰጥና ሊተገበር ይገባል በማለት ይገልፃሉ፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱት የማዳመጥ ትምህርት ይዘቶች እንዴት እየተተገበሩ ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ መፈለግ ሲሆን በጥናቱ ዳሰሳ ላይ በማዳመጥ ትምህርት ላይ የተሰሩ ጥናታዊ ጹሑፎች እንደሌሉና እንደሌሎች ጥናታዊ ጽሑፍ ለምን እንዳልተሰራ መፍትሔ ለማፈላለግ ነው:: ይህም የማዳመጥ ትምህርት ችላ የተባለ የክሂል ዘርፍ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ በ2015 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር  የተዘጋጀው መፅሐፍ ውስጥ ግን ይህ ችግር ተቀርፎ የማዳመጥ ትምህርት ይዘቶች ተካተው በአዲስ መልክ ስራ ላይ ውለዋል፡፡ ነገር ግን የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት የሆነው  ክሂሉ ችላ ተብሎ ከመቆየቱና መፅሀፉ አዲስ ከመሆኑ አንጻር መምህራኑ ክሂሉን እንዴት እየተገበሩት ነው የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ በተመሳሳይ በዚሁ ርዕስ ማለትም በማዳመጥ ክሂል ላይ የተሰሩ ጥናቶች አለመኖራቸውን በማየት ጥናቱ ቢጠና ለሌሎች ክሂሎችና የትምህርት ዘርፎች የጎላ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው በማመን አጥኚዋ ለማጥናት ተነሳስታለች፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በጉራጌ ዞን በመስቃን ወረዳ ውስጥ በተመረጡ 4 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ8ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ትምህርትን የክፍል ውስጥ አተገባበርን መፈተሽ ነው ፡፡ በዚህ የጥናት አላማ ላይ ተመርኩዞ ዝርዝር አላማዎችም እንደሚከተለው በውስጡ ተካተዋል፡፡

1. መምህራኑ የማዳመጥ ትምህርት አተገባበርን በክፍል ውስጥ እንዴት እየተገበሩ እንደሆነ መፈተሽ፣
2. መምህራኑ ስለማዳመጥ ትምህርት ያላቸውን ግንዛቤ መገምገም፣
   3 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አዳምጦ መረዳትን ለማስተማር የሚጠቀሙባቸውን ብልሀቶች ምን እንደሚመስሉ መመርመር፣
4 በማዳመጥ ትምህርት አተገባበር ላይ ያሉ ችግሮችን መፈተሽ እና መለየት ናቸው።

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቃሜታዎች ይኖሩታል።

1. የቋንቋ መምህራን ሊከተሉት የሚገባውን የማዳመጥ ትምህርት አተገባበር ሂደት ይጠቁማል፣ ፍንጭ ይሰጣል።
2. የቋንቋ መምህራን ስለማዳመጥ ትምህርት በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያግዛል።
3. ወደፊት በዚህ ርዕስ ዙሪያ ተመሳሳይ ችግር ይዘው በተለያየ የክፍል ደረጃዎች ላይ ጥናት ለማድረግ ለሚነሱ እንደመነሻ ሊያገለግል ይችላል።

4.መምህራን የሚያስተምሩትን መማሪያ መፅኀፍ እንዲገነዘቡት ያስችላል።

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በጉራጌ ዞን በመስቃን ወረዳ ዉስጥ በተመረጡ 4 የመንግስት የመጀመርያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማለትም በዶቦ ጡጦ በመቂቾ ቁጥር አንድ በአካሙጃ እና በጁኒየር ትምህርት ቤቶች ላይ የተገደበ ነው። ከይዘት አንፃር ሲታይ በ2015 አ.ም ስራ ላይ በዋለው በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅኀፍ ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት አተገባበርን መፈተሽ ላይ ያተኩራል።ስለሆነም ሌሎቹን የቋንቋ ክሂሎች በቀጥታ አይመለከትም።

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. የማዳመጥ ክሂል ምንነት

ስለማዳመጥ ክሂል ምንነት የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎች ሰጥተዋል፡፡ Underwood (1989:1) ‹‹ማዳመጥ በንግግር የተላለፈን አንድን መልዕክት ትኩረት በመስጠት የንግግሩን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት የሚደረግ ጥረት ነው›› በማለት ገልጸዋል፡፡ Kral (1996:189) በበኩላቸው ‹‹ ማዳመጥ ማለት ሰዎች የተናገሩትን ነገር መለየትና መረዳት ማለት ነው›› ይላሉ፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ማዳመጥ ማለት መልዕክት ለመቀበል በትኩረት የምናከናውነው ተግባር መሆኑን ነው››

Grant (1987:76) ስለማዳመጥ ክሂል ሲያብራሩ ማዳመጥ መስማት ማለት አይደለም ማዳመጥ ነገሮችን ለይቶ ማወቅን፣ ማመሳከርን የሚይዝ ነው፡፡ አንድ ሰው ቋንቋ ለመማር መጀመሪያ በህብረተሰቡ የሚነገረውን ስርዓተ ድምጽ፣ ስርዓተ ቃላት ማዳመጥ አለበት በንግግርም ሆነ በውይይት ጊዜ አንዱ የሌላውን ንግግር በሚገባ ካላዳመጠ መግባባት ያዳግታል፡፡በማለት ገልጸዋል፡፡

## 2.2. የማዳመጥ ትምህርት ምንነት

ብዙውን ጊዜ የማዳመጥ ትምህርት የተማሪዎችን ተሳትፎ ያላካተተ እንደሆነ ተማሪዎች መምህሩ የሚለውን ወይም የሚናገውን ወይም በመቅረፅ ድምጽ ላይ የተቀረፀውን በማዳመጥ ደብተራቸው ላይ በማስፈር የሚማሩት (የሚያካብቱት) ክህሎች ተደርጎ ለብዙ ጊዜ ሲሰራበት እንደቆዩ (Brown እና Yule (1983፡56) Anderson እና Lynch (1988:13) ገልፀዋል፡፡ ይህን ሀሳብ Rixon (1986፡1) ሲያጠናክሩት ‹‹የማዳመጥ ክሂል በማህበራዊ ህይወትና ልምድ የሚገኝ ስለሆነ ትምኅርት አያስፈልገውም›› ብለው የሚያምኑ ጥቂቶች እንዳልነበሩ ጠቁመዋል፡፡

ማዳመጥ የመልዕክት ወደ ጆሮ መድረስ ሳይሆን የደረሰውም መልዕክት መረዳትና መተርጎምን የሚያካትት ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪውን ስለማዳመጥ የምናስተምረው የሚያዳምጠውን እንዲያደራጀው፣ እንዲረዳው፣ እንዲተረጉመውና ምላሽ እንዲሰጥ በጥቅሉ በሀሳብ ልውውጡ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡ የማዳመጥ ትምህርት የሚባለውም ተማሪዎችን በዚሁ

መልክ የማዳመጥ ክሂልን ለማለማመድ በክፍል ውስጥ የሚያከናውኑት ተግባራት ነው UnderWood (1989:400) በበኩላቸው ‹‹የማዳመጥ ትምህርት ተማሪውን በማዳመጥ ሂደት ውስጥ ጠንካራ ተሳታፊ የማድረግ ሂደት ነው›› በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይህም ማለት መዋቅራዊና ማህበራዊ የሆነውን አጠቃቀም እንዲሰጥ ማድረግ ነው›› በማለት ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ስለማዳመጥ ትምህርት የተለያዩ አመላካቾች ቢኖሩም ጠቃሚነቱ ግን የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡ በመሆኑም መምህራኑ የማዳመጥ ክሂል ከሌሎች ዘርፎችና ትምህርቶች ጠቃሚ መሆኑን ተረድተው እንዴት መተግበር እንዳለባቸው ማወቅና መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም በአተገባበሩ ወቅት ተገቢውን የማዳመጥ ክሂል አቀራረብ አለመከተል ለክሂሉ መዳበርና ሌሎች የክሂል ዘርፎችና ትምህርት ቤት ለሚኖረው አስተዋጽኦ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ስለዚህ ተፅዕኖውን ለመስበር የማዳመጥ ትምህርት በማዳመጥ ክህሎት ላይ ቁልፍ ሚና እንደሚጫወትና በማንኛውም የቋንቋ ትምህርት ላይ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ Anderson እና Llynch (1986:64) Brown እና Yule (1983:56) እና Grant (1987:17) ይጠቁማሉ፡፡

### 2.2..1. የማዳመጥ ትምህርት አላማ

የማዳመጥ ትምህርት በክፍል ውስጥ የሚሰጥበት ዋና አላማ ተማሪዎችን ጥሩ አድማጭ ለማድረግ ነው፡፡ይህን አስመልክተው Ur (1984:2) ‹‹አልፎ አልፎ ከምናዳምጠው ነገር የምንፈልገውን መረጃ ከማዳመጥ አላማችን ጋር ይገናኛል፡፡ ምክንያቱም የምናዳምጠው አንድ ነገር እናገኛለን ብለን ካላሰብን አናዳምጥም›› በማለት ሲገልጹ ማረው (1989፡124) ደግሞ ‹‹ሰዎች በማዳመጥ ጊዜ መጀመሪያ አላማ ይዘው ከተነሱ የትኩረት አቅጣጫቸውም ሆነ ፍላጎታቸው ለአላማቸው የሚገዛ ይሆናል›› በማለት ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም የማዳመጥ ትምህርት አላማን Grant(1987-20) Underwood(1989:4) Rixon(1986:65) በድሉ (1996፡50) እንደ ሚከተለው ይዘረዝሯቸዋል፣ እነርሱም፤

- ተማሪዎች የተለያዩ ድምጾችን መለየት እንዲችሉ ማድረግ፣
- ድምጾቹ ፣የሀዘን፣ የቁጣና የደስታ መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ማድረግ፣
- የንግግሩን ዋጋ መመዘንና ማድነቅ እንዲችሉ ማድረግ ፣
- የንግግሩን መጨረሻ መተንበይ እንዲችሉ ማገዝ ባደመጡት ነገር ላይ ተመርኩዘው በውይይት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስቻል፣

- መረጃን በመቀበል ተናጋሪዎች ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ ማገዝ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የማዳመጥ ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎች የሚሰሙትን ድምጽ በማቀናጀት የአረፍተነገሩን መልዕክት እንዲረዱ፣ የተናጋሪውን ስሜት እንዲረዱና እንዲገነዘቡ ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡ ማስቻል ነው፡፡

## 2.3 የማዳመጥ ትምህርት ክንዉኖች የአተገባበር ደረጃዎች

የማዳመጥ ክሂል በክፍል ውስጥ ሲቀርብ ሶስት ደረጃዎችን ይከተላል (በድሉ 1996፣ Underwood 1989 እና Rixon 1986) ፡፡ እነዚህም ደረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 2.3.1 ቅድመ ማዳመጥ (pre-listening)

ይህ ደረጃ ተማሪዎች ከሚቀርበው ንግግር /ፅሑፍ/ ጋር ትውውቅ የሚያደርጉበት ነው፡፡ እንዲሁም የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት ሊጠይቁ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ስለሚደመጠው ነገር እንዲገምቱ የሚደርግበት ደረጃ ነው፡፡ Underwood(1989) እንደገለጹት በዚህ የማዳመጥ ደረጃ መምህራን የተለያዩ ሀሳቦችን በማንሳት ተማሪዎች የመነቃቃት ስሜት እንዲፈጥሩ ማድረግ፣ ከትምህርት ርዕስ ጋር የተለያያዙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን መመዘን፣ ተማሪዎች በትምህርቱ ርዕስ ዙሪያ ይነገራል ብለው የሚጠብቁትን ነገር በመጠየቅ እንዲገምቱ ማድረግ፣ ለትምህርቱ የቀረበውን ይዘት በተገቢው መልክ እንዲረዱ የአዳዲስ ቃላት ፍቺን ለተማሪዎች በማሳወቅ ከሚደመጠው የትምህርት ይዘት ጋር ተያያዥነት ያላቸው መርጃ መሳሪዎችን በማቅረብ አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ፣ በማዳመጥ ጊዜ ሊሰሯቸው የሚችሉት ጥያቄዎችና በማዳመጥ ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት እንዴት መስራት እንዳለባቸው አጠር ያለ ማብራሪያ መስጠት ይኖርባቸዋል (Underwood 1989) ፡፡

### 2.3.2 የማዳመጥ ጊዜ ተግባር (while listening)

የማዳመጥ ጊዜ ተግባር ተማሪዎች መምህራኑ የሚነግሯቸውን ወይም የሚያነቡላቸውን ፅሑፍ በትኩረት በማዳመጥ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት የሚመለከት ነው፡፡ የማዳመጥ ጊዜ ተግባር የሚያረጋገጡበት ፣አዳዲስ መረጃዎች የሚሰበሰቡበት እና አዳምጦ የመረዳት ግንዛቤያቸው ከፍ የሚልበት ነው፡፡ የዚህ ተግባር ዋናው አላማም ተማሪዎች ሳይጨነቁና ሳይጠበቡ የሚነበብላቸውን የፅሑፍ መልዕክት እንዲረዱት ማስቻል ተማሪዎቹ ለማዳመጥ መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡

### 2.3.3.ድህረ ማዳመጥ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

ተማሪዎች ባዳመጡት ንግግር ወይም ፅሁፍ መሰረት በሀሳብ መሰማማትና አለመስማማታቸው ወይም ያደመጡትን ከግላዊ ገጠመኝ በማዋሀድ ሊመልሷቸው የሚችሉትን ጥያቄዎች እንደተማሪዎቹ ምንነት በመጠየቅ የማዳመጥ ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት ተግባር ነው፡፡

Rixon (1986,72) በሌላ በኩል እንደሚገልጹት ድህረ ማዳመጥ ተግባር ተማሪዎች የፈለጉትን ወይም የጠየቁትን መረጃ በትክክል ማግኘታቸውን ወይም አለማግኘታቸውን የሚያረጋግጡበት፣ የይዘቱን ርዕስ በጥልቀት ለመመርመርና የተናጋሪዎቹን ዝንባሌ ለማወቅ የሚሞክርበት ደረጃ (ተግባር) ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መምህሩ ምጋቤ ምላሽ (Feed back) በቃል መስጠት፣ ተማሪዎቹ በጥንድ ፣ በቡድንና በጋራ በመሆን መልሶችን እንዲያመሰክሩ ማድረግ በንግግሩ (በተደመጠው ፅሑፍ) ውስጥ ሊያከራክሩ የሚችሉ ነገሮችን በመምረጥ ተማሪዎቹ እንዲከራክሩ ማድረግ፣ ባደመጡት ፅሑፍ ውስጥ የተሰማቸውን ነገር እንዲናገሩ ማድረግ ወዘተ.. በዚሁ ደረጃ ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራት ናቸው:: በአጠቃላይ በማዳመጥ ትምህርት ክንውን ወቅት ከላይ በዘርፉ ምሁራን የተገለጹትን የማዳመጥ ተግባራት ተከትሎ ማስተማር ለማዳመጥ ክሂል ውጤታማነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎችን ውጤታማ ለማድረግ ያስችላል፡፡ስለዚህ ማንኛውም የቋንቋ መምህራን ከላይ የተገለጹትን የማዳመጥ ትምህርት ተግባራት መተግበር ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.4 በማዳመጥ ትምህርት ወቅት የመምህሩና የተማሪው ተግባር

### 2.4.1 በማዳመጥ ትምህርት ወቅት የመምህራን ተግባር

መምህራን የመማር ማተማሩን ሂደት የሚመሩ፣ የተማሪዎችን የመማር እድል የሚፈጥሩና የሚያመቻቹ ናቸው፡፡ በማዳመጥ ትምህርት ጊዜ የተማሪዎችን ፍላጎት ማጎልበት ፣ ተማሪዎቹ የሚያደምጡባቸውን ምክንያቶችና አላማዎች ማሳወቅ፣ በተማሪዎቹ ላይ ማዳመጥ የሚያመጣውን በራስ የመተማመን ስሜት ማሳደር፣ የመምህሩ ሚና መሆኑን Yagang (1993;13) ይገልጻሉ፡፡ እንዲሁም Underwood (1989:21-28) እንደሚሉት በማዳመጥ ሂደት ወቅት ተማሪዎቹን ለተለያዩ የማዳመጥ ሂደት ማጋለጥ፣ ማዳመጡን አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መመስረት ተማሪዎቹ ማዳመጥን ለምን እንደሚረዱአቸው ማሳወቅ እንዲሁም እንዴት ማዳመጥ እንዳለባቸው ማሳወቅና በራስ የመተማመን ስሜት እንዲያድርባቸው ማድረግ

የመምህራኑ ተግባራት እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ተግባራት ከትምህርት በፊትና በትምህርት ጊዜ የሚከናወኑ እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡

### 2.4.2. ከትምህርት በፊት የሚከናወኑ የመምህሩ ተግባራት

በዚህ ወቅት መምህራን ቀደም ሲል ያዘጋጁትን እቅድ መሰረት በማድረግ በክፍል ውስጥ የሚያከናውኑትን ተግባራት በቅደም ተከተል የሚያቀርቡበትና ተማሪዎችን የሚደግፉበት ደረጃ ነው፡፡ በዚህም ጊዜ ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ተግባራት አስመልክተው Underwood (1989; 26-28) ለተማሪዎቹ በየትኛውም ደረጃ ድጋፍ ማድረግ እርስ በርስ እንዲረዳዱ ማበረታታት፣ የትምህርት ጊዜውን ከፈተና የተለየ ማድረግ፣ ማስታወሻ መያዝ እንዳለባቸው መግለጽ፣ በቡድን በጥንድ እንዲሰሩ ማድረግ፣ ምላሹን ወዲያውኑ መስጠት እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች ካዳመጡት ውስጥ መረጃዎችን ቀስመው ማስቀረት እንዲችሉ በክፍል ውስጥ መምህሩ፣ የሚከተሉትን ንኡሳን ክሂሎች ለተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ማለማመድ እንዳለበት ማረው (1998፡13-4) እና በድሉ (1996፡49) እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ፡፡ እነርሱም መምህራን ለተማሪዎች መልዕክቱን ከደራዊ እውቀት ጋር እንዲያገናዝቡ ማድረግ፣ አብይ የሚባሉ ሀሳቦችን እንዲለዩ ማለማመድ፣ በሚያዳምጡበት ወቅት ጥያቄ እንዲጠይቁ ማለማመድና፣ በአትኩሮት ማዳመጥን ማለማመድ፣ ዝርዝር ገለፃዎችንና ማብራሪያዎችን በመጠቀም በአእምሮ ምስል መቅረጽን ማለማመድ፣ ተዛማጅ ሀሳችን በየፈርጃቸው ማደራጀትን ማለማመድ፣ ማስታወሻ መያዝን ማለማመድ ወዘተ… ናቸው፡፡ ስለዚህ መምህራን ተማሪዎቻቸውን እነዚህን ንኡሳን ክሂሎች ተጠቅመው ካለማመዷቸው የማዳመጥ ትምህርት አላማን ያሳካሉ፡፡ ተማሪዎቻቸውንም ጥሩ አድማጭ እንዲሆኑ ያግዛሉ፡፡

### 2.4.3. በማዳመጥ ትምህርት ወቅት የተማሪዎች ተገባር

የማዳመጥ ትምህርት ዋናው አላማ ተማሪዎችን ጥሩ አድማጭ ማድረግና በማህበራዊ ህይወታቸው ውስጥ በሚኖራቸው ግንኙነት ጥሩ ማህበራዊ ተራክቦ እንዲኖራቸው ማድረግ እንደሆነ በተለያዩ ምሁራን ተገልጹአዋል፡፡ በማዳመጥ ትምህርት ወቅት የተማሪዎቹን ተግባር አስመልክቶ Lynch (1983:3-14)ስ ሲገልጹ ተማሪዎች ከዐረፍተነገር ውስጥ ዋናውን ሀሳብ መጨበጥ፣ የመልዕክቱን ጠቃሚነት መገምገም፣ አደረጃጀቱን መገምገም፣ ማስታወሻ መያዝ፣

በውይይትና በክርክር በንቃት መሳተፍ፣ መልመጃዎችን መስራት፣ ምጋቤ ምላሹን መከታተል መሆናቸውን ይነገዘባሉ፡፡

## 2.5 የማዳመጥ ክሂልን ውጤታማነት የሚያሰናክሉ ጉዳዮችና መፍትሔዎቻቸው

- ማዳመጥ በሌሎች የሚነገር መልዕክት በአትኩሮትና በንቃት በማዳመጥ፣ መልዕክቱን የመገንዘብ፣ የመለየት፣ ምላሽ፣ የመስጠትና ማስታወሻ የመውሰድ ሂደት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ክሂል በክፍል ውስጥ ሲተገበር የማዳመጥ ትምህርት ክንውኖች ውጤታማነትን የሚያስናክሉ ጉዳዮች ይከሰታሉ፡፡ እነዚህን ጉዳዮች Boyle (1984-35); Harmer (1991፤212)፣ Ur(1984-7) እና Yagang (1993:17)እንደሚከተለው ያስቀምጧቸዋል፤

እነርሱም የመረጃ መደራረብ፣ የተናጋሪው የሀሳብ ቅንብርም ሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ችግር፣ ፍሬ ነገሮችን የመለየት ብቃት፣ የአካባቢያዊ ሁኔታ ምቹ አለመሆን፣ የተናጋሪው ወይም የአንባቢው የድምጽ ተሰሚነት፣ የሚያዳምጥበት አላማ፣ ለተናጋሪው ያለው አመለካከት፣ ለመልዕክቱ ያለው አመለካከት፣ የአድማጩ እድሜ ጾታ፣ ቤተሰባዊ ደራ፣ ትምህርታዊ ዳራ፣ አካላዊ ጤንነት፣ ውስጣዊህመም፣ ድካም፣ የአእምሮ መረበሽ እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን ውስጣዊና ውጫዊና ችግሮች ተብለው በሁለት ይከፈላሉ ውጫዊ የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡፡

የመረጃ መደራረብ፣ የአካባቢያዊ ሁኔታ ምቹ አለመሆን፣ የተናጋሪ ወይም የአድማጩ የድምጽ ተሰሚነት፣የተናጋሪው ፍጥነትና ማንነት፣ አላስፈላጊ ድግግሞሽ፣ በማዳመጥ ወቅት የሚሰሙ አካባቢያዊ ድምጾች፣ የማስተማሪያ መሳሪያ አለውስጣዊ ችግሮች/እንቅፋቶች/ የሚባሉት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡ አድማጩ ስሜቱን ማስባሰብ አቅቶት በሀሳብ የሚዋልል ከሆነ፣ ለተናጋሪው ያለው አመለካከት፣ ውስጣዊ ህመም፣ ድካም፣ የአእምሮ መረበሽና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### 2.5.1 መፍትሔዎቻቸው

የማዳመጥ ትምህርትን የሚያደናቅፉ ወይም ውጤታማነትን የሚያሰናክሉ ጉዳዮችን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ እንደማይችል Yagang (1993:17) ይገልጻሉ፡፡ ይህ ማለት ግን መምህራን እነዚህን አደናቃፊ ጉዳዮች ለማስተካከል የሚያከናውኑት ተግባር የለም ማለት አይደለም፡፡

ስለዚህ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ምቹ የሆኑ ውህድ አሃዶችን ማዘጋጀትና፣ ጠቃሚ መልመጃዎችን መዘጋጀትና ስነ ልሳናዊ እውቀታቸውን ማሳደግ የይዘቱን ደራ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል በማለት ቶማስ (2002፡20) ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም Yagang(1993;17-19) የሚከተሉትን የመፍትሔ ሀሳቦች አስቀምጠዋል፤

እነርሱም ለተማሪዎቹ ምቹ የሆነ ድግግምሽ የሌለበት ቀላልና አጭር ውህድ አሀድ ማዘጋጀት ስነልሳናዊ እውቀታቸውን በተለያየ መንገድ ማሳደግ፣ የአፈ ፊት ተማሪዎች ቅላጼ ማለማመድ፣ የሰሙትን እንዲደግሙ፣ ማድረግ፣ ጠቃሚ መረጃዎችን ማዘጋጀት፣ የይዘቱን ደራ ማሳወቅ፣ የተማሪዎቹን ንኡሳን ክሂልን ማሳደግ ለምሳሌ (ለተወሰነ መረጃ ማዳመጥ፣ ለዋና ሀሳብ ማዳመጥ የሚፈልገውን ለመረዳት ማዳመጥ፣ የተናጋሪውን አመለካከት ለመረዳት ማዳመጥ ናቸው፡፡

## 2.6 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

መስፍን (2000) ‹‹ በአማርኛ መማሪያ መፅሐፎች ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር የቀረቡ መልመጃዎች ይዘትና አዘገጃጀት ግምገም በ11ኛ እና 12ክፍል ተተኳሪነት›› በሚል ርዕስ ጥናት አቅርቡአል የጥናቱም ውጤት መልመጃዎቹ ከተተግባሪነት፣ ከቅደም ተከተላዊነት፣ ከተገቢነት ወዘተ….. አንጻር የተሻሉ ሲሆኑ ከተሰጠው ጊዜ ከሳቢነትና ከሌሎች ክሂሎች ጋር ከመያያዝ አንጻር ጉድለት ያለበት መሆኑን ጠቅሷል፡፡

እቴነሽ (1986) ‹‹በ9ኛ ክፍል በአማርኛ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች ትንተናና ግምገማ›› የሚል ሲሆን፣ በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት የማዳመጥ ክሂል በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ተገቢውን ትኩረት እንዳላገኘ ይገልጻሉ፡፡

ንጉሴ (1997) ‹‹በትግራይ ክልል ማዕከላዊ ዞን በተመረጡ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል የአማርኛ የማዳመጥ ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ›› ሲሆን ውጤቱም ተማሪዎች ማዳመጥን በተግባር በማለማመድ የሚማሩበት ሁኔታ አለመኖሩን ጠቅሰው የመፍትሔ ሀሳቦችን በመጠቆም ያበቃሉ፡፡

አልማዝ (2006) ‹‹በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ›› የሚል ሲሆን ውጤቱም

የማዳመጥ ክሂል የክፍል ውስጥ ክንውኖች በትክክል እንደማይተገበሩ መምህራኑ የማዳመጥ ንኡሳን ክሂሎችን ለተማሪዎች እንደማያለማምዱ አጋዥ የሆኑ የማስተማሪያ መሳሪያዎችንም እንደማይጠቀሙ ይገልጻሉ፡፡

ቶማስ (2002) ‹‹9ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን የማዳመጥ ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ፍተሻ (በኦሮሚያ ክልል በተመረጡ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት) ሲሆን ውጤቱም መምህራኑ የማዳመጥን ትምህርት ሲያስተምሩ የማዳመጥ ትምህርት ክንውኖችን እንደማይከተሉና በተገቢው መንገድ እንዳልተገበሩት ይገልጻሉ፡፡

ፍቅር (2002) ‹‹በሶዶ ከተማ በሚገኙ በሁለት የመንግስትና በሁለት የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ንጽጽራዊ ግምገማ›› ሲሆን ውጤቱም በመንግስትም ሆነ በግል ትምህርት ቤቶች የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በተሟላ ሁኔታ የማይተገበር መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

ብርቱኳን (2010) ‹‹በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ›› (በተመረጡ አምስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት) ሲሆን ውጤቱም በተጠቀሱት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ እንደማይተገበር ገልጸዋል፡፡

ጥላሁን (2003) ‹‹የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አተገባበር ፍተሻ›› (በሰሜን ወሎ ዞን በተመረጡ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት) የሚል ሲሆን ውጤቱም በተባለው ክፍል የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ እንደማተገበር ገልጸዋል፡፡

ይህ ጥናት ደግሞ ‹‹ በጉራጌ ዞን በመስቃን ወረዳ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ትንተና ››ነው፡፡ ስለዚህ ጥናቱ በመዳመጥ ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ ከላይ ከተገለጹት ጽሑፎች ጋር ቢመሳሰልም በክፍል ውስጥ አተገባበር ትንተና ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ከእቴነሽ፣ ከመስፍን፣ ከፍቅሩ፣ ስራ ይለያል፡፡ ከንጉሴ፣ ከቶማስ፣ ከአልማዝ፣፣ ከብርትኳን ጋር በክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ ያተኮረ በመሆኑ ቢመሳሰልም

የንጉሴ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥ ትምህርት ሲያስተምሩ የሚያስተምሩበት የማስተማር ስነ ዘዴ አመራረጥ ከክፍል ውስጥ አተገባበር ጋር አጣምሮ የያዘ ሲሆን የጥናቱ ተተኳሪዎች ኢ-አፈ ፈት ናቸው፡፡

የቶማስና የብርቱኳን ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በማዳመጥ ትምህርት ወቅት መምህራኖች በየደረጃው የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች ተገቢነት፣ በማዳመጥ ትምህርት ወቅት ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮችና መፍትሔዎቻቸው ከክፍል ውስጥ አተገባበር ጋር አጣምሮ የያዘ ሲሆን የጥናቱ ተተኳሪዎች ኢ-አፈ ፈት ናቸው፡፡

የአልማዝ ጥናት በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶችና ክንውኖች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለመተግበር አመቺ መሆን አለመሆናቸውን የሚፈትሽ ነው፡፡ የፍቅሩ ጥናት ደግሞ በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት አተገባበርን በንጽጽር መፈተሸ ነው፡፡

ይህ ጥናት ግን በጉራጌ ዞን በመስቃን ወረዳ በ8ኛ ክፍል ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት እንዴት ይተገበራል? የሚል በመሆኑ ከሁሉም ጥናቶች ይለያል፡፡ ልዩነቱም ከተመረጠው የክፍል ደረጃ፣ ከተማሪዎቹ ኢ-አፈ ፈትነት ጥናቱ ከተጠናበት ጊዜና ቦታ፣ ከጥናቱ ትኩረት አቅጣጫ አንጻር ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የአጠናን ዘዴ

### 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን የመረጃ ምንጮች አደረጃጀት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አይነትና አደረጃጀት፣ የመረጃ አስባሰብ ዘዴ እና የጥናቱን አጠናን ስልት በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት በ2015 አ.ም ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች መማሪያነት የተዘጋጀው የአማርኛ ቓንቓ መማሪያ መፅነፍ የማዳመጥ ክኂል ይዘት አቀራረብ መገምገምና አተገባበርን መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱም የተከተለው አይነታዊ ምርምር ሲሆን ፣ አሀዛዊ /መጠናዊ/ የምርምር ዘዴን በደጋፊነት ተጠቅሜያለሁ፡፡ አቀራረቡም ገላጭ ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ ይህንንም የጥናት ንድፍ በተመለከተ ያለው (2009፡40) ‹‹ገላጭ ጥናት ተመራማሪው የሚያጠናውን ባህሪ እንዳለ ትርካዊ በሆነ በአንባቢው አእምሮ ውስጥ ስለጉዳዩ ስዕል በሚፈጥር ሁኔታ ባልተጋነነ፣ ባልተሞካሸ፣ ባልተንኳሰሰና እውነታውን በማያደበዝዝ መልክ ለማቅረብ ያስችለዋል›› በማለት ይገልፃሉ፡፡

### 3.2 የናሙና አወሳሰድ

#### 3.2.1 የትምህርት ቤቶች የናሙና አወሳሰድ

ይህ ጥናት በጉራጌ ዞን በመስቃን ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አራት ትምህርት ቤቶች ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት ተመርጠዋል፡፡እነዚህ ትምህርት ቤቶች የተመረጡት በአመቺ ናሙና ስልትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡አራቱም ትምህርት ቤቶች ከአጥኚዋ መኖሪያ ጋር ቅርበት ያላቸው በመሆናቸው መረጃዎችን ለመሰብሰብ ቀላል ይሆናል ብላ በመገመቱአ ነው፡፡የተመረጡት ትምህርት ቤቶች በመስቃን ወረዳ እና በከተማ አስተዳደር የሚገኙ ሲሆኑ አካሙጃ፣ጁኒየር መቂቾ ቁጥር አንድ እና ዶቦጡጦ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡

#### 3.2..2 የክፍል ደረጃ አመዳደብ

ለጥናቱ የተመረጠው የክፍል ደረጃ 8ኛ ክፍል ሲሆን፣ ይህም የሆነበት ምክንያት አጥኚዋ በዚህ የክፍል ደረጃ አማርኛን የሚያስተምሩ መምህራን የማዳመጥ ክሂል ትምህርትን መተግበር

አለመተግበራቸውን ለመፈተሽ እንዲያመች ጥናቱን በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ በመከተል ነው፡፡

### 3.2..3 የምድብና የተማሪዎች ናሙና

በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የክፍል ምድቦች ብዛት በጁኒየር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት 4 በመቂቾ ቁጥር 1 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት 7 ፣ በዶቦ ጡጦ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት 2 እና በአካሙጃ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት 1 በድምሩ 14 የ8ኛ ክፍል ምድቦች ይገኛሉ፡፡ እነዚህንም ምድቦች በጥናቱ ለማካተት አስቸጋሪ ስለሆነ በቀላል የእጣ ናሙና ዘዴ ከአራቱ ትምህርት ቤቶች አንድ አንድ ምድቦች ተመርጠዋል፡፡ በተጨማሪም ለናሙናነት በተመረጡት ምድቦች በመማር ላይ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል ውስጥ በአማካይ ከ50 እስከ 60 ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ከእያንዳንዱ ክፍል ግማሽ/50%/ በታች ያህሉ በጥናቱ ለማካተት ሲባል ከየክፍሉ 20 በድምሩ 80 ተማሪዎች በጥናቱ ተካተዋል፡፡ እነዚህም ተማሪዎች በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ተለይተው የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡

### 3.2..4 የመምህራን አመራረጥ

በጉራጌ ዞን በመስቃን ወረዳ ውስጥ በተመረጡ አራት የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የ8ኛ ክፍልን የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን 4 ሲሆኑ እነዚህም መምህራን የእያንዳንዳቸውን ትምህርት ቤት ይወክላሉ በማለት ጠቅላይ የናሙና ዘዴን በመጠቀም ሁሉም በጥናቱ ተካተዋል፡፡

## 3.3 የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በዚህ ጥናት ውስጥ የሚካተቱ ትምህርት ቤቶች መምህራንና ተማሪዎች መረጣ ከተከናወነ በኃላ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተመርጠዋል፡፡ እነዚህም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎች ውስጥ ምልከታና የፅሑፍ መጠይቅ በማዘጋጀት ነው፡፡ከእነዚህም መካከል ምልከታ በዋናነትጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን የፅኁፍ መጠይቅ ደግሞ በአጋዥነት አገልግሉአል፡፡

### 3.3.1.ምልከታ

በዚህ ጥናት በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረግ ምልከታ የመረጃ ማግኛ መንገዶች ሁለት ሲሆኑ እነርሱም ተሳታፊና ኢ-ተሳታፊ ይባላሉ፡፡ በተሳታፊነት የሚደረግ ምልከታ አጥኚው በክፍል ውስጥ በሚከናነው ተግባር ተሳታፊ በመሆን የሚያከናውነው ሲሆን፣ በኢተሳታፊነት የሚደረግ ምልከታ ደግሞ አጥኚው በድርጊቱ ተሳታፊ ሳይሆን መረጃ ለመሰብሰብ ብቻ በክፍል ውስጥ ተገኝቶ የሚያካሄደው የምልከታ ሂደት ነው፡፡ ለዚህ ጥናት በዋናነት ተግባራዊ የሆነውም ኢ-ተሳታፊነት ምልከታ ነው፡፡ በዚህ ኢ-ተሳታፊነት ምልከታ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ መተግበር ያለመተግበራቸውን በተዘጋጀው የመከታተያ ቅጽ አማካይነት በማየት ምልከታ ተደርጓል፡፡ የመከታተያ ቅጹ የተዘጋጀው ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ከተገለጸው ጽንሰ ሀሳብ በመነሳት በእለቱ የሚቀርበውን የማዳመጥ ትምህርት ክንውን ቅደም ተከተላዊ አቀራረብ ለመከታተል በሚያመች ሁኔታ የተዘጋጀ ነው፡፡ የቀረቡትም ጥያቄዎች ‹‹አዎ›› አልፎ አልፎ›› እና ‹‹የለም››የሚል አማራጭ መልሶችን ይዟል፡፡ አባሪ ‹‹ሀ›› ን ይመልከቱ፡፡ የምልከታ ቅጹ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በአማካሪዬ ተገምግሞ አስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡

በምልከታው ወቅትም የሚገኘው ውጤት ከአጥኚዋ ግላዊ አመለካከትና ተጽዕኖ የፀዳ እንዲሆንና ውጤቱም አስተማማኝ እንዲሆን በማሰብ ሁለት የምልከታ አከናዋኞች እንዲኖሩ ተደርጓል፡፡ እነዚህ የምልከታ አከናዋኞች የአማርኛ መምህራን ሲሆኑ፣ የስራ ልምዳቸውም ከ2 እስከ 12 አመት ነው፡፡ ከእነዚህ መምህራን ጋር ምልከታው ከመከናወኑ በፊት ስለ አሰራሩና ቅጽ አሞላሉ ውይይት ተደርጓል፡፡ መረጃውም ተሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት ለናሚናነት በተመረጡት 4 መምህራን ላይ በአጠቃላይ ሶስት ሶስት በአጠቃላይ አስራ ሁለት ምልከታ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም በምልከታው ዙሪያ ውይይት በማድረግ የተገኘው ውጤት ተደምሮ አማካዩ ለትንተና ቀርቧል፡፡

### 3.3.2.የፅሁፍ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት የተመረጠው ሌላኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የፅሑፍ መጠይቅ ሲሆን፣ የፅሑፍ መጠይቁም በጥናቱ በተመረጡ 4 ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች የሚሞላ ነው፡፡

ለመምህራኑ የተዘጋጀው የፅሑፍ መጠይቅ ሶስት ክፍሎች ሲኖሩት የመጀመሪያው የመምህራኑን ዳራ የሚመለከት ሲሆን ሁለተኛውና ሶስተኛው ክፍል ደግሞ የመምህራኑን የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርን በተመለከተ በዝግና በክፍት ጥያቄዎች የቀረበ ነው። አባሪ‹‹ለ››ን ይመልከቱ። ለተማሪዎቹ የተዘጋጀው የፅሑፍ መጠይቅ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍት መጠይቅ እና ሁለተኛው ደግሞ ዝግ ጥያቄዎችን የያዘነው አባሪ ‹‹ሐ›› ን ይመልከቱ። የመምህራኑም ሆነ የተማሪዎቹ የፅሁፍ መጠየቅ የማዳመጥ ክሂል ክንውኖችን /ደረጃዎችን/ የክፍል ውስጥ አተገባበርን አስመልክቶ ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢ የሆኑ ጥናቶች የተጠቀሙበትን መጠየቅ እንደ ሞዴል በመውሰድ ከጥናቱ ጋር እንዲስማማ ተደርጎ ተዘጋጅቷል። ልክ እንደ ምልከታ ቅጹ የፅሑፍ መጠይቁም አማካሪዬ ጋር ቀረቦ ማሻሻያ ተደርጎበታል። በዚህም መሰረት የተዘጋጀው መጠይቅ ለ4 መምህራንና ለ80 ተማሪዎች ተሰራጭቶ መረጃው እንዲሰበሰብ ተደርጓል።

## 3.4 የመረጃ ትንተና

በዚህ ጥናት ከምልከታ እንዲሁም ከጽሁፍ መጠይቅ ከመምህራንና ከተማሪዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በቁጥርና በመቶኛ ተቀምረው፣ በሰንጠረዥ ተዘጋጅተው በገለጻ ወይም ‹‹በአይነታዊ›› መተንተኛ ዘዴ ተተንትነው ቀርበዋል። ተያይዞም የተገኘው መረጃ ተተርጉሞ ማብራሪያ ተሰጥቶበታል። በተጨማሪም ከአንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ከተገኘው ምላሽ ከሌላው ጋር ያለው ትስስሮሽ እየተጠና ደረጃ በደረጃ ተተንትኖ ቀርቧል፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና እና የውጤት ትንተና

## 4.1 የመረጃ ትንተና

በምዕራፍ አንድ ላይ እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋናው አላማ በጉራጌ ዞን በመስቃን ወረዳ በተመረጡ አራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ2016 ኢ.ም በተዘጋጀው በ8ኛ ክፍል ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካቱት የማዳመጥ ክሂል ትምህርት አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡

ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ ፣ በበቂ ሁኔታ ለመገምገምና የተሟላ መረጃ ለማግኘት ያስችል ዘንድ ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡
ከእነዚህም የመረጃ መሰቢሰቢያ መሳሪያዎች ውስጥ የክፍል ውስጥ ምልከታ ዋነኛው ሲሆን፣ የተማሪዎችና የመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ ደግሞ በተጨማሪነት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በዚህም መሰረት የተሰበሰበው መረጃ ውጤት ከዚህ በታች ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

## 4.2 የጥናቱ ውጤት ማበራሪያ

በምነራፍ አንድ ላይ እንደተገለፀው ይህ ጥናት የተካሄደው ለ--ጥያቄዎች መልስ በመስጠት የጥናቱን አላማውች ከግብ ለማድረስ ነው፡፡በተደረገው ጥናትም ጥቄዎቹ መልስ ስካገኙ አላማዎች ተሳክተዋል፡፡የጥናቱ መልስ የተገኘው ከምልከታና ከፅኑፍ መጠይቅ ሲሆን ትንተናው መሰረት ያደረገው የውጥት ማብራሪያ ከዚ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

### 4.2.1 የተጠኚ መምህራን እና ተማሪዎች ዳራ

### 4.2..2. የተጠኚ መምህራን ዳራ

ለመምህራን በቀረበው የፅሁፍ መጠይቅ መሰረት የመምህራን ዳራዊ ሁኔታ ማለት የመምህራን የትምህርት ደረጃ ፣ የአገልግሎት ዘመን ፣ ፆታ፣ የምያስተምሩት የትምህርት ደረጃ ፣የምያስተምሩት የክፍል ደረጃ ፣ የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ ፣ የትምህርት ቤቱ ስም ፣ዕድሜ ወዘተ የሚፈትሹ ጥያቄዎች በማቅረብ መልስ ተሰቶባቸዋል፡፡ ውጤቱም እንደሚከተለው ቀጥለን ከዚህ በታች እንመለከታለን፡፡

ሰንጠረዥ 1 :- የመምህራንን ዳራዊ ሁኔታ የሚያሳይ

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | የተሰጠኚ መምህራን ዳራ እና የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመምህራን ስም | መ1 | መ2 | መ3 | መ4 |
| 2 | ዕድሜ | 28 | 60 | 35 | 35 |
| 3 | ፆታ | ሴ | ሴ | ወ | ወ |
| 4 | የምያስተምሩበት የክፍል ደረጃ | ከ5 — 8ኛ | 8ኛ | 7ኛ እና 8ኛ | 7ኛ እና 8ኛ |
| 5 | የአገልግሎት ዘመን | 8 | 40 | 10 | 10 |
| 6 | የትምህርት ደረጃ | ዲፕሎማ | ዲፕሎማ | ዲግሪ | ዲፕሎማ |
| 7 | የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ አብይ | አማርኛ | አማርኛ | አማርኛ | አማርኛ |
| | ንዑስ | -- | እንግሊዘኛ | እንግሊዘኛ | እንግሊዘኛ |

ከሰንጠረዥ አንድ እንደምንረዳው የጥናቱ ተሳታፊዎች ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ አራት መምህራን ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ 2 ወንዶች ሲሆኑ 2 ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ እድሜያቸው ከ28 እስከ 60 አመት ሲሆን በመምህርነት ሙያ ከ8 አመት እስከ 40 አመት ያገለገሉ ናቸው፡፡ የትምህርት ደረጃቸውም 1 መምህር የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ሲሆን 3 መምህራን ደግሞ ዲፒሎማ አላቸው፡፡ እንዲሁም የምያስተምሩበት የትምህርት ደረጃ መ1 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የምትገኘው መምህር ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል የምታስተምር ሲሆን፣ መ2 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት 8ኛ ክፍል፣ በመቀኾ መ3 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እና መ4 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት 7ኛ እና 8ኛ ክፍልን የሚያስተምሩ ናቸው፡፡አራቱም መምህራን አማርኛን በአብይ የሰለጠኑ ሲሆን ሶስቱ

መምህራን ደግሞ እንግሊዘኛን በንዑስ ሰልጥነዋል፡፡ አንዷ ደግሞ በንኡስ የሰለጠነችበት እንደሌላት ገልፃለች፡፡

በተጨማሪም ከዚህ ቀደም በምዕራፍ ሦስት ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ለጥናቱ በተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የአማርኛ መምህራን ብዛት በትምህርት ቤት አንድ ሲሆን በአጠቃላይ አራት መምህራን መጠይቁን እንደሞሉ ተደርገው አራቱም ሞልተው ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የክፍል ምልከታውንም ለማከናወን ቀና ትብብር በማድረግ በእቅዱ መሰረት እያንዳንዳቸው ሶስት ሶስት ጊዜ በአጠቃላይ አስራ ሁለት ጊዜ የክፍል ውስጥ ምልከታ ለማድረግ ተችሏል፡፡

### 4.1.2 የተጠኚ ተማሪዎች ዳራ ነክ ጉዳዮች መግለጫ

በዚህ ክፍል የተማሪዎች የትምህርት ደረጃ ፣ የሚማሩበት ትምህርት ቤት ስም ፣ ለጥናቱ በተመረጡ ትምህር ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት ፣ ለጥናቱ የተመረጡ ናሙና ተማሪዎች ብዛት እና መጠይቁን በትክክል የሞሉ ተማሪዎች ብዛት ጥያቄዎች ቀርበው ምላሽ ተሰቶባቸዋል፡፡ ውጤቱም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 2፡- የተማሪዎች ዳራዊ ሁኔታ የሚያሳዩ**

| ተቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | በጥናቱ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች | ለናሙናው የተመረጡ ተማሪዎች ብዛት | መጠይቁን በትክክል የሞሉ ተማሪዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አካሙጃ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት | 56 | 20 | 20 |
| 2 | ጁኒየር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት | 50 | 20 | 20 |
| 3 | መቂቾ ቁጥር አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት | 50 | 20 | 20 |
| 4 | ደቦ ጡጦ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት | 50 | 20 | 20 |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደምንረዳው በምዕራፍ 3 ላይ እንደተገለፀው በየትምህርት ቤቱ ካሉ ምድቦች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት በአማካይ አንድ ክፍል ውስጥ ከ 50- 56 ነው፡፡ ከእነዚህም ተማሪዎች ውስጥም ከአንድ ምድብ ከግማሽ በታች ያህሉን በናሙናነት ለማጠቃለል ሲባል በየትምህርት ቤቶች ካሉ አንድ አንድ ምድቦች 20 በድምሩ 80 ተማሪዎችን በመምረጥ መጠይቁን እንደሞሉ ተደርጓል፡፡ መጠይቁንም ሁሉም ተማሪዎች ሞልተው መልሰዋል፡፡

## 4.2 በ2015 ዓ/ም ሥራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ መልመጃዎች ብዛት

ይህ ጥናት በ8ኛ ክፍል ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት አተገባበርን መተንተን ሲሆን፣ በ2015 ዓ/ም በታተመው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ ያሉ የመልመጃ ብዛትና የይዘት ክፍሎች ምን ያህል እንደሆኑና ከእነዚህም መልመጃዎች ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ስንት መልመጃዎች እንዳሉት ከእነዚህም ውስጥ ምልከታው ምን ያህሉን እንዳጠቃለለ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 3 ፡- በ2015 ዓ/ም ስራ ላይ የዋለው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃፍት ውስጥ የሚገኙ መልመጃዎች ብዛትና የይዘት ክፍሎች የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| የመልመጃዎቹ ይዘትና ክፍል | የመልመጃዎች ብዛት | |
|---|---|---|
| | በቁጥር | በ% |
| መፃፍ | 10 | 16.6 |
| ሰዋ ሰው | 10 | 16.6 |
| ቃላት ፍቺ | 10 | 16.6 |
| ማንበብ | 10 | 16.6 |
| መናገር | 10 | 16.6 |
| ማዳመጥ | 10 | 16.6 |

ከላይ ከተገለፀው ሰንጠረዥ እንደምንረዳው የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ ያሉ መልመጃዎች ብዛትና ይዘት ክፍሎች የቃላት ፍቺ፣ የማንበብና የመፃፍ ፣ የሰዋሰው ፣ የመናገርና የማዳመጥ ይዘት 60 መልመጃዎች ያላቸው ሲሆን የመናገር 10 ፣ የቃላት ፍቺ 10 ፣የማዳመጥ 10 ፣ የማንበብ 10 ፣ የሰዋሰው 10 የመፃፍ 10 መልመጃዎች ያሏቸው ሲሆን መልመጃዎች እኩል ይዘት ቢኖራቸውም ማዳመጥን ለማስተማር ከተዘጋጀው

ይዘት አንፃር ሲታይ ዝቅተኛ መሆኑን ለመረዳት ችለናል፡፡ ስለዚህ ማዳመጥን ለመሸፈን የተሰጠው ቦታ ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ በዚህ ጥናት የማዳመጥ ክሂል ትምህርት እየተተገበረ እንደሆነ ለመፈተሽ ከተጠቀመባቸው የመረጃ መሰቢሰቢያ ውስጥ አንዱ ምልከታ ነው፡፡ በመሆኑም በመፅሐፍ ውስጥ ከሚገኙት 10 የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች ውስጥ 2 መልመጃዎች ብቻ በምልከታ የተፈተሹ ሲሆን ቀሪዎቹ 8 መልመጃዎች በጊዜ እጥረት ሳቢያ በጥናቱ ሊካተቱ አልቻሉም፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ትንተና የቀረቡ መረጃ ውጤትም በእነዚህ 2 ምልከታዎች ወቅት የተገኙትን መረጃዎች መሰረት ያደረገ ነው፡፡

## 4.3 መምህራንና ተማሪዎች ስለማዳመጥ ክሂል ትምህርት ያላቸው አመለካከት ፍተሻ

### 4.3.1 መምህራን ስለማዳመጥ ክሂል ያላቸው አመለካከት ፍተሻ

**ሰንጠረዥ** 4 ፡- መምህራን ስለማዳመጥ ክሂል ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምላሽ ፍተሻ

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | የለም | | አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | የማዳመጥ ክሂል አተገባበርን አስመልክቶ የተለያዩ ስልጠናዎችን ለማግኘት የተመቻቸሎት ጊዜ አለ? | - | - | 4 | 100 | -- | - |
| 2 | የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ መተግበሩ አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ? | 4 | 100 | - | - | - | - |
| 3 | *የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲቀርብ ተማሪዎች በንቃት ይሳረፋሉ?* | - | - | - | - | 4 | 100 |
| 4 | ማዳመጥን ለማስተማር ከተቋማት ያገኙት እውቀት በቂ ነው ብለው ያምናሉ? | - | - | 4 | 100 | - | - |

ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው በጥያቄ 1 እና 4 ያስቀመጧቸው መልሶች አሉታዊ ሲሆኑ፣ የሚጠቀሙትም መምህራን ስለማዳመጥ ክሂል ትምህርት አተገባበር አስመልክቶ የተለያዩ ስልጠናዎችን እንደማያገኙና ከዚህ በፊትም ማዳመጥን ለማስተማር ያገኙት እውቀት በቂ አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በጥያቄ 2 ያስቀመጧቸው መልሶች አዎንታዊ ሲሆኑ

መምህራኑ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ መቅረቡ ጠቃሚ መሆኑን ሲያምኑ ተማሪዎች ደግሞ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲቀርብ ፈፅሞ በንቃት እንደሚሳተፉብ ጥያቄ 4 ላይ ገልፀዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው መምህራን ማዳመጥን ሲያስተምሩ ተማሪዎች ትኩረት ሰጥተው በንቃት እንዲሳተፉ በአተገባበሩ ላይ በቂ ዝግጅት ማድረግ እንዳለባቸውና እንደሚያስፈልግ ይስማሙበታል፡፡

### 4.3.2 የተማሪዎች ስለማዳመጥ ክሂል ትምህርት ያላቸው አመለካከት

**ሰንጠረዥ 5፡-** ተማሪዎች ስለማዳመጥ ክሂል ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምላሽ ትንተና

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | የለም | | አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ መቅረቡ አስፈላጊ ነው ብለሽ/ህ//ታምኛለሽ/ህ | 39 | 48.75 | 30 | 37.7 | 11 | 13.77 |

ከሰንጠረዥ እንደምንገነዘበው ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ መቅረቡ አስፈላጊ ነው፡፡ የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው 39 ( 48.75% ) ያህሉ አስማማለሁ 30 (37.7 % ) ያህሉ የለም ሲሉ 11 (13.77%) ደግሞ አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ በሰንጠረዡ የሚያመላክተው መረጃ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ መቅረቡ የሚያስማማቸው ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ30 (37.7% ) ያህሉ የሰጡት ምላሽ ደግሞ አሉታዊ ነው ፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ መቅረቡ አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝበው መምህራን የማዳመጥ ክሂል ትምህርትን ለተማሪዎች ለማቅረብ ይችሉ ዘንድ ትምህርቱን ሳቢና ማራኪ ማድረግ ከ መምህራን የሚጠበቅ ሌላ የስራ ድርሻ እንደሚኖረው ነው፡፡

## 4.4 የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ ተግባራት አፈፃፀም

ለተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የሚሰጥባቸው አንዱ ምክንያት በተማሪዎች መካከል የሚከናወነውን የማዳመጥ ችሎታ እንዲኖራቸው ለማስቻልና ተማሪዎች በሌሎች የቋንቋ ክሂሎችና የትምህርት አይነቶች አጥጋቢ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ለማድረግ ክሂሉ በተገቢው መንገድ ሊሰጥ እንደሚገባ ይታመናል፡፡ ስለሆነም የዚህ ክሂል የክፍል ውስጥ ተግባራት የሚተገበሩት በመምህራንና በተማሪዎች ሲሆን አተገባበራቸው በሶስት ደረጃዎች የተከፈሉ

ናቸው። እነርሱም ቅድመ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም ፣የማዳመጥ ጊዜ ክንውን አፈፃፀምና የድህረ የማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም ናቸው። ስለዚህ እያንዳንዱን ተግባራት በየትምህርት ቤቶች ያላቸውን አፈፃፀም ከዚህ በታች እንመለከታለን።

### 4.4.1 የቅድመ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም

የቅድመ ማዳመጥ ክንውን ለማዳመጥ ትምህርት ተብሎ የሚቀርበው ፅሁፍ ከመነበቡና ተማሪዎች ከማዳመጣቸው በፊት እንዲነቃቁ፣ በርዕስ ጉዳዩ ላይ ፍላጎት እንዲያድርባቸው በትምህርቱ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያግዝ ቅድመ ክንውን ተግባር ነው። የዚህ ክንውን ዋናው አላማም ተማሪዎች ስለሚባለው ነገር ለማዳመጥ ዝግጁ፣ ለትምህርቱ ነቅተው እንዲገኙ ለማድረግ ነው። ይህን ሀሳብ መሰረት በማድረግ በቅድመ ማዳመጥ ጊዜ ክንውን ወቅት በእያንዳንዱ ትምህርት ቤቶች የተካተተውን የምልከታ ውጤት እንደሚከተለው ይቀርባል።

ሰንጠረዥ 6፦ **ስለቅድመ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም ከክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘ ምላሽ ትንታኔ**

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | የለም | | አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1.1 | ርዕሱን አስተዋውቀዋል? | 20 | 100 | - | - | - | - |
| 1.2 | ተማሪዎችን አነቃቅተዋል? | 20 | 100 | - | - | - | - |
| 1.3 | ከዚህ በፊት በርዕሡ ዙሪያ የሚያውቁት ጉዳይ እንዳለ የቀደመ እውቀታቸውን ገምግመዋል? | 20 | 100 | - | - | - | - |
| 1.4 | በርዕሱ ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ነገሮች እንዲገመቱ አድርገዋል? | 20 | 100 | - | - | - | - |
| 1.5 | የማዳመጥ ትምህርቱን ከማንበባቸው በፊት ተማሪዎች ለማዳመጥ ዝግጁ መሆናቸውን ጠይቀው አረጋግጠዋል? | - | - | 20 | 100 | - | - |
| 1.6 | ከማዳመጥ ትምህርቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃ መሳሪያ አዘጋጅተዋል? | - | - | 20 | 100 | - | - |
| 1.7 | ለማዳመጥ ትምህርት ካቀረቡት ይዘት ወስጥ የአዳዲስ ቃላት ፍቺ ለተማሪዎች አስተዋውቀዋል? | - | - | - | - | 20 | 100 |

ከሰንጠረዥ ስድስት፡- እንደሚገነዘበው የቅድመ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀምን አስመልክቶ በተደረገ ምልከታ መምህራን የማዳመጥ ይዘት ክንውንን ከማቅረባቸው በፊት የዕለቱን

የማዳመጥ ትምህርት ርዕስ በማስተዋወቅ ተማሪዎችን አነቃቅተዋል ፡፡ በርዕሱ ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ነገሮችን እንዲገምቱ አድርገው የቀደመ ዕውቀታቸውን ገምግመዋል፡፡ ይሁን እንጂ የማዳመጥ ይዘቱን ከማንበባቸው በፊት ተማሪዎች ዝግጁ መሆናቸውን ሳያረጋግጡና ከማዳመጥ ትምህርቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መርጃ መሳሪያዎችን ሳያዘጋጁ ወደ ማዳመጥ ጊዜ ክንውን እንደሚሸጋገሩ ጠቁመዋል ፡፡ይሁን እንጂ ለማዳመጥ ትምህርት ካቀረቡት ይዘት ውስጥ ቃላት ፍቺ ለተማሪዎች በመሆኑም በቅድመ ማዳመጥ ክንውን ወቅት መምህራን ትኩረት ሊያደርጉባቸው የሚገቡ ተግባራት ባለመስማማታቸ እንደሚያስተዋውቁ መዘንጋታቸውን ተመልክተናል፡፡ ለምሳሌ ከዕለቱ ትምህርት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መርጃ መሣሪያዎች በማዘጋጀት ረገድና ለማዳመጥ ትምህርት በቀረበው ይዘት ውስጥ የአዳዲስ ቃላት ፍቺ ለተማሪዎች በማስተዋወቅ ተማሪዎችን ለማዳመጥ ትምህርት ሲያዘጋጁ አልታዩም ፡፡ በመሆኑም ይህ ክንውን የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት የማያነሳሳ (የማይቀሰቅስ) ከመሆኑም አንፃር ተማሪዎችን ለቀጣዩ የማዳመጥ ጊዜ ክንውን ዝግጁ የማያደርግ አሰራር ነው፡፡

ሰንጠረዥ 7 ፡- **ስለ ቅድመ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም ከመምህራን የፅሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽና ፍተሻ**

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | የለም | | አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | የዕለቱ የማዳመጥ ትምህርት ርዕስ በቃል በመግለፅና በጥቁር ሰሌዳ በመፃፍ ያስተዋውቃሉ? | 4 | 100 | - | - | - | - |
| 2 | በርዕሱ ዙሪያ ከዚህ በፊት የሚውቁት ጉዳይ እንዳለ በመጠየቅ የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት ይገመግማሉ? | 2 | 50 | - | - | 2 | 50 |
| 3 | በርዕሱ ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ሀሳቦችን እንዲሁም እድል ይሰጣሉ? | 4 | 100 | - | - | - | - |
| 4 | ለማዳመጥ ትምህርት የቀረበውን ይዘት በተገቢው መልኩ እንዲረዱ የአዳዲስ ቃላት ፍቺ ለተማሪዎች ያስተዋውቃሉ? | - | - | 4 | 100 | - | - |
| 5 | ከዕለቱ ትምህርት ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃ መሳሪያ አዘጋጅተዋል? | 2 | 50 | - | - | 2 | 50 |
| 6 | የማዳመጥ ይዘት ከማንበባቸው በፊት ለተማሪዎች ለማዳመጥ ዝግጁ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ? | 4 | 100 | - | - | - | - |

ከሰንጠረዥ እንደተመለከትነው ሁሉም መምህራን ርዕሱን ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍና በቃል በመግለፅ አስተዋውቀዋል፡፡ በርዕሱ ዙሪያ ደግሞ ከዚህ በፊት የሚያውቁት ጉዳይ እንዳለ በመጠየቅ የተማሪዎችን የቀድመ እውቀት እንደሚገመግሙ፣ በርዕሱ ዙሪያ ሊነሱ ስለሚችሉ ሀሳቦች እንዲገምቱ እድል እንደሚሰጡና የማዳመጥ ይዘቱን ከማንበባቸው በፊት ተማሪዎች ለማዳመጥ መዘጋጀታቸውን እንደሚያረጋግጡ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ነገር ግን ለማዳመጥ ትምህርት ሲዘጋጁ ተማሪዎች በርዕሱ ዙሪያ የሚያውቁት ጉዳይ እንዳለ የቀድመ እውቀታቸውን የሚገመግሙትና መርጃ መሳሪያዎችን የሚቀሙት ግን እማይስማሙ በመሆኑ ለማዳመጥ ክሂል ትምህርት ስኬታማነት እንቅፋት ሆኗል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ መምህራን ለማዳመጥ ክሂል ትምህርት የቀረበው ይዘት በተገቢው መልኩ እንዲረዱ የአዳዲስ ቃላት ፍቺ ለተማሪዎች የሚያስተዋውቁበት ምንም አጋጣሚ አለመኖሩን ከሰንጠረዥ በተገኘው መረጃ ለማግኘት ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 8 ፡- ስለቅድመ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ፍተሻ**

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | የለም | | አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | መምህራቹ የእለቱን ትምህርት ርዕስ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍና በቃል በመግለፅ ያስተዋውቋችኂል? | 72 | 90 | - | - | 8 | 10 |
| 2 | በርዕሱ ዙሪያ ከዚህ በፊት የምታውቁት ጉዳይ እንዳለ የቀደመ እውቀትታችሁን ተጠቅማችሁ እንድትመልሱ ይጠይቋችኂል? | 19 | 23.75 | 28 | 35 | 33 | 41.5 |
| 3 | በርዕሱ ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ሀሳቦችን እንድትገምቱ እድል ይሰጧችኃል? | 31 | 38.70 | - | - | 49 | 61.25 |
| 4 | ለማዳመጥ ትምህርት የቀረበውን ይዘት በተገቢው መልኩ እንድትረዱ የአዳዲስ ቃላት ፍቺ ያስተዋውቋችኂል? | 37 | 46.25 | 31 | 38.70 | 12 | 15 |
| 5 | ከዕለቱ ትምህርት ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃ መሳሪያ አዘጋጅተው መምህራቹ ያቀርቡላችኂል? | - | - | 16 | 20 | 64 | 80 |
| 6 | የማዳመጥ ይዘት ከማቅረባቸው በፊት ለማዳመጥ ዝግጁ መሆናችሁን ይጠይቁችኂል? | 64 | 80 | 10 | 12.5 | 6 | 7.5 |
| 7 | በማዳመጥ ጊዜ የምትሰሯቸውን ጥያቄዎች ቀድመው በመስጠት እንዴት መስራት እንዳለባችሁ ማብራሪያ ይሰጧችኃል? | - | - | 80 | 100 | - | - |

ከዚህ ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ በተገኘው ምላሽ መሰረት መምህራን የማዳመጥ ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ ርዕሱን ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍና በቃል በመግለፅ እንደሚያስተዋውቋቸው ሲጠየቅ 72 (90%) ያህሉ እስማማለሁ ያሉ ሲሆን 8 (10 %) ያህሉ ደግሞ አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ከሰንጠረዥ ከተገኘው ከተማሪዎች መልስ የምንገነዘበው መምህራን ርዕሱን ከማስተዋወቅ አንፃር የተሻለ አተገባበር እንዳላቸው ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም ከምልከታና ከፅሁፍ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ ጋር ሲነፃፀር ተቀራራቢ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡

ለማዳመጥ ትምህርት በቀረበው ርዕስ ዙሪያ ከዚህ በፊት የቀደመ እውቀት ተጠቅመው እንዲመልሱ መምህራን ያግዟቸው እንደሆነ ተጠይቀው 33 (41.5 %) ያህሉ ደግሞ አልስማማም ሲሉ 28 (35 %) ያህሉ የለም እና 19(23.75%) ያህሉ ደግሞ እስማማለሁ የሚል ምላሽ ተጥተዋል፡፡

በዚህ መረጃ መሰረት ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸውን በመጠቀም በቀረበው ርዕስ ዙሪያ ሀሳብ ማፍለቅ እንዲችሉ የማድረግ ተግባራትን እያከናወኑ እንደሆነ ቢጠቁሙም ያን ያህል ውጤታማ እንዳልሆኑ ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ከመምህራን ምልከታና ከፅሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ደግሞ መምህራኑ ይህን ተግባር እንደማያከናውኑ ያስረዳል፡፡በተፀማሪም መምህራን በርእሱ ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ሀሳቦችን እንዲገምቱ እድል እንደሚሰጣቸው ሲጠየቁ 31(38.70 %) ያህሉ እስማማለሁ 49(61.25 %) ያህሉ ደግሞ አልስማማም ብለው መልሰዋል፡፡ይህም መምህራኑ በርእሱ ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ሀሳቦችን አዘውትረው ሳይሆን እንደማይስማሙ ከመረጃው ለማወቅ ተችሉአል፡፡ ሌላው መምህራን በማዳመጥ ጊዜ የሚሰራቸውን ጥያቄዎች ቀድመው በመስጠት እንዴት መስራት እንዳለባቸው ምንም አይነት ማብራሪያ እንደማይሰጣቸው ከተማሪዎች ከተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሉአል፡፡

በተጨማሪ መምህራን ተማሪዎቻቸውን የቀድመ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙበትና በቀረበላቸው ርዕስ ዙሪያ የተለያዩ ሰሃቦች ማፍለቅ እንዲችሉ በማድረግ ተግባራትን እያከናወኑ እንደሆነ መረጃው ይጠቁማል፡፡ነገር ግን ከመረጃው ለመረዳት እንደተቻለው ውጤቱ አጥጋቢ እንዳልሆነ ያመለክተናል፡፡ ነገር ግን ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅና ከምልከታ የተገኘው መረጃ መምህራን እነዚህን ተግባራት እያከናወኑት እንዳልሆኑ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡

ከመረጃው መረዳት እንደሚቻለው መምህራን ለተማሪዎቻቸው የማዳመጥ ይዘት ከማቅረባቸው በፊት ተማሪዎችን በርዕሱ ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ሀሳቦችን እንዲገምቱ እድል እንደሚሰጧቸው ከተሰጠው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም መረጃ ከመምህራኑ የፅሑፍ መጠይቅና ከምልከታ ከተገኘው ውጤት ጋር ተቀራራቢነት እንዳለው ያመለክታል፡፡

መምህራን ከዕለቱ ትምህርር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃ መሣሪያ ይጠቀማሉ ? የሚል ጥያቄ ተማሪዎች ተጠይቀው 16 (20 %) የለም ያህሉ ሲሆን 64 (80 %) ያህሉ አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ከዚህ መረጃ የምንገነዘበው መምህራን ለተማሪዎቻቸው በመረጃ መሣሪያ የተደገፈ ትምህርት የማይስማሙ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም ውጤት ከመምህራን የፅሁፍ መጠይቅና ከምልከታ ከተገኘው ውጤት ጋር ልዩነት እንዳለው ለመረዳት ተችሏል፡፡

መምህራን ለተማሪዎቻቸው የማዳመጥ ይዘቱን ለማስተማር ከመዘጋጀታቸው በፊት ዝግጁ እንዲሆኑ ይጠይቋቸው እንደሆነ ተጠይቀው 64 (80 %) ያህሉ አዎ ያሉ ሲሆን 10 (12.5 %) ያህሉ የለም ያሉ ሲሆን 6 (7.5 %) ደግሞ ያህሉ አልስማማም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ መረጃ ለመገንዘብ እንደተሞከረው አብዛኛው መምህራን ማዳመጥን ከማቅረባቸው በፊት ተማሪዎች ዝግጁ እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው ነው፡፡

በአጠቃላይ ከመምህራን የቅድመ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀምን ስንመለከት ከመምህራንና ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅና ከምልከታ በተገኘው መረጃ መሰረት ግማሽ መምህራን ይዘቱን ከማቅረባቸው በፊት ለተማሪዎቻቸው እድል እንደሚሰጧቸው ተጠቁሟል ፡፡ ግማሽ መምህራን ደግሞ የማዳመጥ ይዘትን ለማስተማር መረጃ መሣሪያ እንደማይጠቀሙ እንደማይስማሙ ተጠቁሟል፡፡ ይህም የቅድመ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀምን በተሳካ ሁኔታ እንዳይተገበር በማድረጉ የተማሪዎችን ተሳትፎ ሊቀንስ ችሏል፡፡

### 4.4.2 የማዳመጥ ጊዜ ክንውን አፈፃፀም

የማዳመጥ ጊዜ ክንውን መምህራን ለተማሪዎች የሚያነቡላቸው ፅሑፍ ወይም የሚነግራቸውን ነገር በትኩረት በማዳመጥ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት የሚመለከት ሲሆን በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተገለፀው የማዳመጥ ጊዜ ክንውን ዋናው አላማ ተማሪዎች ሳይጨነቁ

የሚነበብላቸውን ፅሑፍ መልዕክት እንዲረዱ ማስቻል ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከመምህራን፣ ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅና ከምልከታ የተገኘው ምላሽ ትንተና እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 9፡- ስለማዳመጥ ጊዜ ክንውን አፈፃፀም ከክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘ ምላሽ ፍተሻ**

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለው | | የለም | | አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | በማዳመጥ ጊዜ ንባቡን ሲያቀርቡ ቆም እያሉ ቀጥሎ ምን ሲሆን እንደሚችል ተማሪዎች እንዲገምቱ ያደርጋሉ? | 4 | 100 | - | - | - | - |
| 2 | የማዳመጥ ይዘቱን ሲያነቡ ለተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲሰሩ በቂ ጊዜ በመስጠት አንቀፃችን በእርጋታና በድጋሚ ያነባሉ? | - | - | 4 | 100 | - | - |
| 3 | መምህራኑ ፅሑፍን ለተማሪዎቻቸው ያነበቡባት ሁኔታ ማራኪነት አለው? | 4 | 100 | - | - | - | - |
| 4 | ተማሪዎች የሚያዳምጡትን ምንባብ ከራሳቸው የህይወት ልምድ ጋር እንዲያዛምዱ ያደርጋሉ? | - | - | 4 | 100 | - | - |

ከሰንጠረዡ የምንረዳው ሁሉም መምህራን የማዳመጥ ጊዜ ክንውኖችን በተገቢው ሁኔታ እንዳልፈፀሙት ነው ፡፡በተደረገው ተከታታይ ምልከታ እንደተገነዘብነው ሁሉም መምህራን ምንባቡን ሲያነቡ ቆም እያሉ ቀጥሎ ምን ሊሆን እንደሚችል ተማሪዎች እንዲገምቱ የሚያደርጉ መሆናቸውንና መምህራኑ ፅሁፉን ለተማሪዎች ሲያነቡ ማራኪነት እንዳለው መገንዘብ ተችሏል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ተማሪዎች የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ በቂ ጊዜ ሰጥተው አንቀጻችን በእርጋታና በድጋሚ ከማንበብ አንፃር ያላቸውን አፈፃፀም የተሟላ እዳልሆነ ከመረጃው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም መምህራን ተማሪዎች ጥያቄዎችን ስለሚሰሯቸው በቂ ጊዜ ሳይሆን የሚያስጨንቃቸው ምባቡን አንብበው ስለሚጨርሱት ጊዜ ላይ

ነው  ትኩረት ሲያደርጉ የታዩት። በተጨማሪ ምንባቡን ደጋግመው ለማንበብ እንዳልሞከሩ ነው።

መምህራን ለተማሪዎች የሚነበብላቸውን ምንባብ ከራሳቸው የህይወት ልምድ እና ተሞክሮ ማዛመድ እንዳልቻሉ ነው። ይህም መምህሩ ምንባቦችን ከተማሪዎች  የህይወት ልምድ ጋር ማለማመድ እንዳለባቸው ይጠቁማል። ስለዚህ መምህሩ ለቀጣይ ትልቅ ስራ እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልገዋል።

**ሰንጠረዥ 10 ፡- ስለማዳመጥ ጊዜ ክንውን ከመምህራን የፅሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ፍተሻ**

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | የለም | | አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 10.1 | በማዳመጥ ጊዜ ንባቡን ሲያቀርቡ ቆም እያሉ ቀጥሎ ምን ሊሆን እንደሚችል ተማሪዎች እንዲገምቱ ያደርጋሉ? | 4 | 100 | - | - | - | - |
| 2 | የማዳመጥ ይዘቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲሰሩ በቂ ጊዜ በመስጠት አንቀፃችን በእርጋታና በድጋሚ ያነባሉ? | 4 | 100 | - | - | - | - |
| 3 | ተማሪዎች የሚያደምጡትን የምንባብ ከራሳቸው የህይወት ልምድ ጋር እንዲያዛምዱ ያደርጋሉ? | 2 | 50 | - | - | 2 | 50 |

ከሰንጠረዡ መረጃ ለማግኘት እንደተሞከረው ስለማዳመጥ ጊዜ ክንውን አፈፃፀም ከመምህራን በፅሑፍ መጠይቅ በተጠየቁት መሰረት አብዛኛው መምህራን የማዳመጥ ጊዜ ክንውንን ይተገብሩት እንደሆነ ሲገልፁ አንዳንዶቹ ደግሞ ከክፍል ምልከታው በተገኘው መረጃ ደግሞ እየተገበሩት እንዳልሁነ ለመረዳት ተችሏል።

**ሰንጠረዥ 11 ፦ ስለ ማዳመጥ ጊዜ ክንውን አፈፃፀም ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ፍተሻ**

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | የለም | | አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | መምህራኑ በማዳመጥ ጊዜ ንባቡን ሲያቀርቡ ቆም እያሉ ቀጥሎ ምን ሊሆን እንደሚችል እና እንድትገምቱ እድል ይሰጧችኋል? | 53 | 66.25 | 15 | 18.75 | 12 | 15 |
| 2 | የማዳመጥ ይዘቱን ሲያቀርቡ ጥያቄዎችን እንድትሰሩ በቂ ጊዜ ሰጥተው አንቀጾችን በእርጋታና በድጋሚ ያነቡላችኋል? | 22 | 27.5 | 48 | 60 | 10 | 12.5 |
| 3 | የምታደምጡትን ምንባብ ከራሳችሁ የህይወት ልምድ ጋር እንድታዛምዱ ያደርጓችኋል? | 20 | 25 | 49 | 61.25 | 11 | 13.7 |

ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው መምህራን ለተማሪዎች በማዳመጥ ጊዜ ንባቡን ሲያቀርቡላቸው ቆም እያሉ ቀጥሎ ምን ሊሆን እንደሚችል እድል ይሰጧችኃል ተብለው ሲጠየቁ 53 (66.25%) እስማማለሁ ፤ 15 (187.5%) የለም ቀሪዎቹ 12 (15%) ደግሞ አልስማማም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ምላሽ እንደምንረዳው መምህራኑ የማዳመጥ ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ በተሻለ ሁኔታ እንደሚተገብሩት ነው፡፡ ይህ የተማሪዎች ምላሽ ከመምህራኑ የፅሑፍ መጠይቅ መልስ ጋር ተቀራራቢነት እንዳለው ያመላክታል፡፡

መምህራኑ ጥያቄ ለመስራት በቂ ጊዜ ይሰጧችሁ እንደሆነና በእርጋታ በመድገም ያነቡላችኃል? ለሚሉት ጥያቄ 22 (27.7%) እስማማለሁ 48(60%) የለም እና ቀሪዎቹ 10 (12.5% ) አልስማማም የሚል መልስ መስጠታቸውን ከመረጃው ለማግኘት ተችሏል፡፡ ይህ የሚያመለክተው መምህራኑ ንባቡን ሲያቀርቡ በቂ ጊዜ እንደማይሰጧቸው በእርጋታና በድጋሚ እንደማያነቡላቸው ነው፡፡ ይህም ክንውኑን በተሟላ ሁኔታ እንደማይተገብሯቸው ነው፡፡

የምታደምጡት ምንባብ ከራሳችሁ የህይወት ልምድ ጋር እንድታዛምዱ ያደርጓችኋል? የሚል ጥያቄ ተጠይቀው 20( 25%) እስማማለሁ ፤ 49 (61.25%) የለም እና ቀሪዎቹ 11(13.7%) አልስማማም ብለዋል፡፡
ከዚህ መረጃ የምንረዳው መምህራኑ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲተገበሩ የሚያደምጡት ምንባብ ከራሳቸው የህይወት ልምድ ጋር እንደማያዛምዱ ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም ከምልከታ ውጤት ጋር የመመሳሰል ጉዳይ ይታይበታል፡፡

በአጠቃላይ መምህራን በማዳመጥ ጊዜ ክንውን ወቅት ለተማሪዎች የሚደመጠውን ንባብ ሲያቀርቡ ቆም እያሉና ቀጥሎ ምን ሊሆን እንደሚችል እንዲገምቱ በማድረግ በተጨማሪም ፅሑፍን በእርጋታና በመድገም ምንባቡን ከራሳቸው ሀሳብ ጋር እንዲያዋህዱ ማድረግ እንዳለባቸው ይጠቁመናል፡፡ ነገር ግን መምህራኑ ይህን ተግባር ለማከናወን ከእውቀት ነፃ እንደሆኑ ይጠቁመናል፡፡

### 4.4.3 የድህረ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም

በዚህ የማዳመጥ ክንውን ወቅት በዕለቱ ለማዳመጥ በቀረበው ምንባብ መነሻነት የቅድመ ማዳመጥና የማዳመጥ ጊዜ ተግባራት ከተከናወኑ በኋላ የሚተገበር ነው፡፡ የዚህ የድህረ ማዳመጥ ክንውን ትምህርት ዋና አላማው ተማሪዎች በማዳመጥ ሂደት ውስጥ መተግበር ያላቸውን መተግበራቸውን ለማረጋገጥ መገንዘብ ያላባቸውን ጉዳይ ካልተገነዘቡ ለመመርመር የተናጋሪውን መልዕክት መረዳት እንዲችሉ ለማድረግና ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማስተማር እንደሆነ ባለፈው ምዕራፍ ማለትም በምዕራፍ ሁለት ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም የድህረ ማዳመጥ ትምህርት ክንውን አፈፃፀም በትምህርት ቤቶች እንዴት እየተተገበረ እንደሆነ ከዚህ በታች ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

ሰንጠረዥ 12፦ **ስለ ድህረ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም ከክፍል ምልከታ የተገኘ ምላሽ ፍተሻ**

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | የለም | | አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | ተጠማሪ መልመጃዎች ይሰጣሉ? | - | - | 12 | 100 | - | - |
| 2 | ካዳመጡት ምንባብ ጋርተያያዥነት ያላቸውን ፅሁፎችን እንዲያነቡ ያዛሉ? | - | - | 12 | 100 | - | - |
| 3 | ተማሪዎች ባደመጡት ነገር ላይ በግል፣በቡድን ሆነው እንዲወያዩ ፣ እንዲከራከሩ እድል ይፈጥራሉ? | 9 | 75 | - | - | 3 | 25 |
| 4 | ለተማሪዎች መልሶችን በፅሁፍና በቃል ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉ? | - | - | | | 12 | 100 |

ከሰንጠረዥአስራ ሁለት ላይ ከቀረበውመረጃመረዳትእንደተቻለውመምህራኑ በድህረ ማዳመ ጥ ክንውን ጊዜ የፈፀሙአቸው ተግባራት በቂ አለመሆኑን ከመረጃው ለማወቅ ተችሉአል፡፡ የድህረ ማዳመጥ ክንውን ተማሪው በቅድመ ማዳመጥና በድረ ማዳመጥ ጊዜ ክንውን የተገነዘባቸውን፣የተረዳውን ነገሮች ከሌሎችክሂሎች ጋር በማቀናጀት ሀሳቡን የሚገልፅጽበት፣የሚያዳብርበት ነው፡፡ከላይ እንደተረዳነው መምህራኑ ተማሪዎቹ ያዳመጡትን ነገር በግል፣በቡድን እንዲወያዩ እና የተማቸውን እንዲናገሩ፣እንዲፅፉ፣እንዲወያዩና እንዲከራከሩ ጥሩ እንቅስቃሴ ለማድረግ ሞክረዋል፡፡ቢሆንም ግን ክፍተት ያሉባቸውን የድህረ ማዳመጥ ክንውኖች ክፍተቶቻቸውን ለማየት ሞክረዋል፡፡ስለሆነምክፍተቶች ያሉባቸውን ክሂሎች ለማዳበርም መምህራን ለተማሪዎቻቸው ተጨማሪ መልመጃዎችን መስጠት፤ ካነበቡላቸው ምንባቦች ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ፅሑፎችን እንዲያነቡ ማገዝ አለባቸው፡፡በአጠቃላይ መምህራኑ እነዚህን የማዳመጥ ክንውኖች በክፍል ውስጥ እያከናወኗቸው እንዳልሆነ በክፍል ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለዚህ መምህራን ለቀጣይ ጉድለት የታየባቸውን ተግባራት መፈፀም እንዳለባቸው አቅጣጫ ይጠቁማል፡፡

**ሰንጠረዥ 13 ፦ ስለ ድህረ ማዳመጥ ክንውን ከመምህራን የፅሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ፍተሻ**

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | የለም | | አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | ተጨማሪ መልመጃዎችን ይሰጣሉ? | - | - | - | - | 4 | 100 |
| 2 | ካዳመጡት ነገር/ምንባብ / ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ፅሑፎች እንዲያነቡ ያዛሉ? | 4 | 100 | - | - | - | - |
| 3 | ተማሪዎች ባደመጡት ነገር ላይ በግልወይም በቡድን ሆነው እንዲወያዩ ፤ እንዲከራከሩ እድል ይፈጥራሉ? | 4 | 100 | - | - | - | - |
| 4 | ለተማሪዎች መልሶችን በፅሁፍና በቃል ምጋቤ ምላሽ ይሰጧሉ? | 4 | 100 | - | - | - | - |
| 5 | ተማሪዎች ባደመጡት ነገር ውስጥ የተሰማቸውን እንዲፅፉና እንዲናገሩ ያደርጋሉ? | 4 | 100 | - | - | - | - |

ከዚህ ሰንጠረዥ መረጃ ለመረዳት እንደተቻለው አብዛኛው መምህራን አዎ በማለት የድህረ ማዳመጥ ጊዜ ክንውን ተግባራትን በተሟላ ሁኔታ እያከናወኑ መሆኑን ከሰንጠረዡ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ነገር ግን አራቱም መምህራን ተጨማሪ መልመጃዎችን አልስማማም የሚል መልስ እንደሰጡ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት መምህራኑ ትኩረታቸውን በማዳመጥ ጊዜ ባቀረቡት መልመጃዎች ላይ በመሆኑና ትኩረት ስለማያደርጉ ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 14 ፦ ስለ ድህረ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ፍተሻ**

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | | የለም | | አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | ካዳመጣችሁትም ምንባብ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ፅሑፎችን እንድታነቡ ያደርጓችኃል? | 61 | 76.25 | 4 | 5 | 15 | 18.75 |
| 2 | ካደመጣችሁት ነገር ውስጥ የተሰማችሁን እንድትፅፉ /እንድትናገሩ /ያደርጓችኃል? | 20 | 25 | 40 | 50 | 20 | 25 |
| 3 | ተጨማሪ መልመጃዎችን ይሰጧችኃል? | 30 | 37.5 | - | - | 50 | 62.5 |
| 4 | ለመልሶቻችሁ በቃል ወይም በፅሁፍ እርማት ይሰጧችኃል? | 70 | 87.5 | - | - | 10 | 12.5 |
| 5 | ባደመጣችሁት ነገር ተመስርታችሁ በግል ወይም በቡድን ሆናችሁ እንድትሳተፉ ፤ እንድተወያዩ እና እንድትከራከሩ ያደርጓችኃል? | 72 | 90 | - | - | 8 | 10 |

ከዚህ ሰንጠረዥ አስራ አራት ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው መምህራን ካደመጡት ምንባብ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ፅሑፎችን እንዲያነቡ እንደሚያደርጓቸው ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው ጠንካራ ትጋትና ክትትል እያደረጉ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ካደመጡት ነገር ውስጥ የተሰማቸውን እንዲፅፉ ወይም እንዲናገሩ እንደማያደርጓቸው ተጠቁሟል ይህም የመምህራኑን ስልቹነት እና የተማሪዎችን በራስ ሀሳብን መግለፅ እዳይችሉ እንደማያበረታቷቸው ነው፡፡ ተጨማሪ መልመጃዎችንም ለመስጠት አልእማማም የሚል መልስ እንደሚሰጧቸው ነው፡፡ ይህም ተማሪዎችን ለማብቃት አጥጋቢ እንዳልሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

መምህራን ለተማሪዎች በቃል ወይም በፅሁፍ እርማት እንደሚሰጧቸው ከተገኘው መረጃ ለማግኘት ተችሏል ፡፡ ይህም የመምህራኑን ጠንካራጎን ያላቸው የሚያመለክት መሆኑን ነው፡፡

ተማሪዎች ባደመጡት ነገር ተመስርተው በግል ወይም በቡድን እንዲወያዩ፤ እንዲከራከሩና እንዲሰሩ እንደሚያደርጓቸው ተገልፃል፡፡ ከዚህ የምንረዳው መምህራን የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚመሩት ወይም የሚያከናውኑት መምህር ተኮር ሳይሆን ተማሪ ተኮር እንደሆነ ከተገኘው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከመምህራን፣ ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅና ምልከታ ከተገኘው መረጃ ጋር ሲነፃፀር ካዳመጡት ነገር ውስጥ የተሰማቸውን እንዲናገሩና እንዲፅፉ በግልና በቡድን እንዲወያዩ እና እንዲከራከሩ እንዲሁም እንዲሰሩ ከማድረግ አንፃር ተመሳሳይነት ያለው መረጃ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ የተማሪዎች የፅሁፍ ምላሽና የመምህራን የፅሁፍ መልስ ጋር ሲነፃፀር ደግሞ መልመጃዎችን ከመስጠት አንፃር የተለየ ሲሆን ከሌሎች የድህረ ማዳመጥ ክንውን አፈፃፀም አንፃር ግን ተቀራራቢነት አለው፡፡ በሌላ በኩል ተጨማሪ መልመጃን ከመስጠት ተዛማጅ ፅሑፎችን ከማንበብና ከማዛመድ አንፃር ሲታይ ከተማሪና ከፅሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ጥሩ መሰረት አለው ቢባልም ከተማሪና ከመምህራን ምልከታ የተገኘው መረጃ ግን ይህን አያመለክትም ሆኖም መምህራን ለተማሪዎቻቸው የፅሑፍና የቃል እርማት ከመስጠት አንፃር ከምልከታ በተገኘው ምላሽ እንደማይስማሙ ይጠቁማል፡፡

በአጠቃላይ ከመምህራን፣ ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅና ከምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚያስገነዝበው ከሆነ መምህራን ሶስቱንም የማዳመጥ ክንውኖች አፈፃፀም በበቂና በተመሟላ ሁኔታ እንደማይተገብሩት ነው፡፡

## 4.5 በማዳመጥ ትምህርት ወቅት ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች እና መፍትሔዎቻቸው፡-

የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲተገበር ተፅዕኖ የሚያሳድሩ በርካታ ጉዳዮች እንዳሉ በምዕራፍ ሁለት ላይ ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ ይሁን እንጂ ተፅዕኖዎችን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ባይቻልም መቀነስ እንደሚቻል ከመምህራን የፅሑፍ መጠይቅ ከተገኘ ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም የማዳመጥ ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ ሲተገበር ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ምንድናቸው? በማለት መምህራን በተጠየቁት ጥያቄ መሰረት የሰጡት መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የተማሪዎች የመማር ፍላጎት ወይም ተነሳሽነት ማነስ፤ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ከመጠን በላይ መብዛት ፤ የማዳመጥ ይዘቶች ሳቢ አለመሆን፤ የውጫዊ ድምጾች ትኩረት ተማሪዎችን መሳብ፤ መምህራን የማዳመጥ ምንባብ ሲያነቡ አጋጣሚዎችን ተጠቅመው መረበሽ እና ያልተገቡ ስራዎችን ወይም ተግባራት

መፈፀምና የመሳሰሉ ችግሮች በምልከታ የታዩ ችግሮች ናቸው። ተፅዕኖ ለሚያሳድሩ ጉዳዮች መፍትሔዎች ምን መሆን አለባቸው የሚለውን ጥያቄ በማንሳት ከመምህራን የተገኘው ምላሽ የሚከተለውን መልስ እናገኛዋለን።

- የተማሪዎች የክፍል ጥምረት ተመጣጣኝነት ቢኖረው ፤
- የማዳመጥ ይዘቱን ሲያስተምሩ የተለያዩ ዘመናዊ የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችን ለመጠቀም ቢሞክሩና ይዘቱ ስልቹነት እንዳይኖረው ማድረግ ቢችሉ፤
- በአካባቢ ላይ ሊረብሹ የሚችሉ ድምፆችን ለማጥፋት ባይሞክሩም ራቅ እዲል ቢያደርጉ፤
- ተማሪዎች የተለያዩ አጋጣሚዎችን ተጠቅመው ከመረበሽ ቢቆጠቡ የሚሉ የመፍትሔ ሀሳቦችን ሰንዝረዋል። ነገር ግን መምህራን ካላቸው ሚና አንፃር የሚፈጠሩትን ችግሮች ትኩረት ሰጥተው ለመቅረፍ እንዳልቻሉና ጥረት ሊያደርጉ እንዳልቻሉ ጠቁመዋል። ግን መምህራን ቁርጠኝነት ካላቸው የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያውኩ ጉዳዮችን የተሳካና የተቃና ሁኔታን መፍጠር ይችላሉ። ይሁን እንጂ የተማሪዎች የክፍል ጥምርታ ቁጥር መብዛትን ለማስተካከል ባይችሉም ትምህርት ቤቶች ተጨማሪ ክፍሎችን በማሰራት የተማሪ ቁጥሮችን ዝቅ ካደረጉ የሚፈጠሩ ችግሮችን ማስወገድ ይቻላል። ከዚህ ውጭ ከላይ የተዘረዘሩትን ነገሮች ለመቅረፍ በመምህራን ዘንድ የጎላ ችግሮች እንዳሉባቸው ለማወቅ ተችሏል። ስለዚህ ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ እንደተቻለው የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር በርካታ ችግሮች እንዳሉትና መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች መሆኑን ከምልከታ ከመምህራንና ተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ ለመሰብሰብ ተችሏል።

# ምዕራፍ አምስት

# የማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳቦች

## 5.1 ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና አላማ በጉራጌ ዞን በመስቃን ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ በተመረጡ አራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርን መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን ስለማዳመጥ ክሂል ትምህርት ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል? የማዳመጥን ትምህርት ሲተገብሩ የሚታዩ ችግሮች ምድናቸው? የማዳመጥ ትምህርት ክንውኖችን እንዴት እየተገበሩ ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት የማዳመጥ ትምህርት ክፍለ ጊዜውን በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ፈትሸዋል፡፡ ይህ ፍተሻም የተከናወነው በመምህራንና ተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅና በምልከታ ነው፡፡

ከነዚህም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኘው ምላሽ ፍተሻ ውጤት ሲጠቃለል የሚከተለውን ይመስላል፡፡

- ❖ መምህራኑ የማዳመጥ ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማቅረብ የራሳቸውን የማስተማር ብቃት ማሳደግ እንደሚኖርባቸው ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ጥናት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው መምህራኑ ይህንን ክሂል ለማስተማር በተለያዩ ስልጠናዎች በንባብ ሆነ በልዩ ልዩ መደበኛ ልምድ ልውውጦች ውጭ ያዳበሯቸው ተጨማሪ እውቀቶች እንደሌሉና ባገኟቸው ስልጠናዎችም ያካበቷቸው እውቀቶች የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር በቂ እንዳልሆነ ከመረጃው ለማግኘት ተችሏል፡፡
- ❖ መምህራን ይህን ክሂል ለተማሪዎች ሲያቀርቡ ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ በራሱ የተለየ ዝግጅትና አቀራረብ እንደሚያስፈልገውና በተጨማሪም ክሂሉ እንደሌሎቹ የስነ ልሳን ትምህርቶች በክፍል ውስጥ መቅረቡ አስፈላጊ እንደሆነም ያምናሉ፣ ይስማማሉ፡፡
- ❖ አዳምጦ የመረዳት ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲተገበር አብዛኞቹ ተማሪዎች በአትኩሮት የማዳመጥ ተግባርን እንደማያከናውኑ ነው፡፡ ይህም ተግባር ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዲረብሹና የተረጋጋ የመማር ማስተማር ሥራ እንዳይተገር አድርጓል፡፡ መምህራን ሶስቱንም የማዳመጥ ክንውኖች በክፍል ውስጥ ሲተገበሩ አንዱ ያለ አንዱ ዋጋ እንደሌላቸውና ጥብቅ ትስስር እንዳላቸው በምዕራፍ ሁለት ስር ተገልፀል፡፡ በመሆኑም መምህራን እነዚህን የማዳመጥ ትምህር ክንውኖች በተሟላ ሁኔታ እየተገበሩት እንዳልሆነ ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በተጨማሪም መምህራን በድህረ ማዳመጥ ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራትን ማለትም ተማሪዎችን ጥያቄ በመጠየቅ ማነቃቃት ፤ በርዕሱ ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ነገሮችን እንዲገምቱ ማድረግ፤ የማዳመጥ ርዕሱን ማስተዋወቅ ምንባቡን ማንበብ የመምህራን ጠንካራ ጎኖች እንደሆኑ ተገልፃል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ለተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲሰሩ በቂ ጊዜ ሰጥተው በእርጋታና በድጋሚ ምንበብ፤ ከዕለቱ ትምህርት ጋር የሚስማማ መርጃ መሳሪያ ማዘጋጀት ፤ የማዳመጥ ምባቡን ከራሳቸው የህይወት ልምድ ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግ ፤ ተጨማሪ መልመጃዎችን መስጠት፤ ካዳመጡት ነገር ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ፅሁፎች እንዲያነቡ ማዘዛ ወዘተ----የሚሉ ተግባራት እየተከናወኑ እንዳልሆነና መምህራን ለቀጣይ እነዚህን ተግባራት ሊያሻሽላቸው የሚገቡ ጉዳዮች እንደሆኑ ከመረጃው ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ❖ በማዳመጥ ትምህርት ወቅት ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች እንዳሉ ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ነገር ግን እንዚህን ችግሮች ለመቀነስና ለመቆጣጠር መፍትሔዎችም እንዳልታጡ ነው፡፡ የማዳመጥ ትምህርት ክሂልን በክፍል ውስጥ ሲተገበር ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ ነገሮች ውስጥ የተማሪዎች እና የመምህራን የክፍል ጥምርታ/ቁጥር አለመመጣጠን ፤ ከክፍል ውጭ የሚሰሙ ድምፆች የተማሪዎች የመማር ፍላጎት ማነስ፤ ቢሆኑም መምህራን እነዚህን በክፍል ውስጥ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ ባይችሉም ከእነዚህ ውስጥ የማስተካከልና መቅረፍ የሚችሉአቸውን ችግሮች በማስተካከል ጥረት አለማድረጋቸውን ከመረጃው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ ደግሞ የመምህራኑን ደካማ ጎኖችን የሚያሳዩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

## 5.2 የመፍትሔ ሀሳቦች

የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲተገበር የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ ከፍ ለማድረግ እና አላማውን ከግብ ለማድረስ ሲባል በክፍል ውስጥ ሲቀርብ የተለያዩ ተግባራትንና ክንውኖችን ደረጃ በደረጃ የሚያልፍ በመሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ተግባራትና ክንውኖች እርስ በርስ በመጋመድ የተማሪዎችን የማዳመጥ ችሎታ የሚፈለግበት ደረጃ የሚያደርሱ በመሆናቸው ነው፡፡ ስለዚህ አጥኚዋ በጥናቱ የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ሀሳቦች አቅርባለች፡፡

- መምህራን በመደበኛ ስልጠናቸው ያገኛቸውን እውቀቶች በተለያዩ ስልጠናዎችና ልምምዶች በማድረግ እውቀታቸውን ይበልጥ ሊያዳብሩት እና ሊያጎለብቱት ይገባል፡፡ ስለዚህ የመምህራንን እውቀት ለማሳደግ የመንግስት አካላት ስልጠናዎችን ማመቻቸት እንዲችሉ

ቢደረግ ይህ ደግሞ የመምህራንን የሙያ ማሻሻያ ስልጠና በመስጠት እውቀታቸውን ለማዳበርና ለማስተማር ስልቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ጠቃሚ ስለሆነ ነው፡፡

- መምህራን በየእለቱ በሚያቀርቡት የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ላይ በቂ ዝግጅት ቢያደርጉ፤
- መምህራን ከይዘቱ ጋር ተቀራራቢ የሆኑ ምንባቦችንና መልመጃዎችን እንዲሁም ለተማሪዎቻቸው ተጨማሪ መልመጃዎችንም ቢሰጡ፤
- መምህራን ለማዳመጥ ትምህርት ይዘት የሚመጥኑና ይዘቱን ተአማኒ ለማድረግ የተለያዩ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችን ለመጠቀም ቢሞክሩ፤
- መምህራን ለተማሪዎቻቸው የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ ተማሪዎች የእለቱን ትምህርት ስለመከታተላቸው የተለያዩ የአይን እንቅስቃሴ በማድረግና የድምፅ ቅላፄዎችን በመቀያየርና በማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን የማዳመጥ ትኩረት ለመሳብ ቢሞክሩ፤
- መምህራን ሶስቱንም የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ክንውኖችን ደረጃ በደረጃ በተሟላ ሁኔታ ለመተግበር ቢሞክሩ፤
- መምህራን በአካባቢ የሚገኙትንና በማዳመጥ ትምህርት ወቅት ተፅዕኖ የሚያሳድሩትን ጉዳዮች በመለየትና ከአካባቢያቸው ላይ ለማጥፋትና ለመቀነስ ቢሞክሩ፤
- የተማሪዎች የማዳመጥ ትኩረት ሊስቡ የሚችሉና በማዳመጥ ትምህርት ወቅት በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥሩትን ለማዳመጥ እንቅፋት የሚሆኑ ድምፆችን ለማጥፋት ወይም ለመቀነስ ቢሞክሩ የማዳመጥ ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር የተሳካ ያደርገዋል በማለት አጥኚዋ ታምናለች፡፡

# ዋቢ ፅሑፎች


መስፍን ደፈረሱ፡፡ (2000)፡፡ "የአማርኛ መማሪያ መፅሀፎች ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ መልመጃዎች ይዘትና አዘገጃጀት ግምገማ በ11ኛ እና 12ኛ ክፍል ተተኳሪነት፡፡" በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በድህረ ምረቃ መርሃ ግብር የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነ-ዘዴ፣ 2ኛ ዲግሪ ማሟያነት የተዘጋጀ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

ማረው ዓለሙ፡፡ (1998)፡፡*የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ፡*ባህርዳር፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996)፡፡ *በስነ ፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ብርትኳን ይመር፡፡ (2010)፡፡ ‹በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርግምገማ››(በተመረጡአምስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)

ቶማስ ዳኛቸው፡፡ (2002)፡፡ "የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን የማዳመጥ ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ፍተሻ በኦሮሚያ ክልል በተመረጡ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተካሪነት፡፡" በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በድህረ ምረቃ መርሃ ግብር የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነ-ዘዴ፣ 2ኛ ዲግሪ ማሟያነት የተዘጋጀ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

ንጉሴ ትኩዕ፡፡ (1997)፡፡ "በትግራይ ክልል ማዕከላዊ ዞን በተመረጡ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል የአማርኛ የማዳመጥ ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ፡፡" በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በድህረ ምረቃ መርሃ ግብር የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነ-ዘዴ፣ 2ኛ ዲግሪ ማሟያነት የተዘጋጀ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

አልማዝ አለማየሁ፡፡ (2006)፡፡ "በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍውስጥ የቀረቡት የማዳመጥ ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ በሶስት የአዲስ አበባ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ናሙናነት፡፡" በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በድህረ ምረቃ መርሃ ግብር የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነ-ዘዴ፣ 2ኛ ዲግሪ ማሟያነት የተዘጋጀ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

እቴነሽ ተገኝ፡፡ (1986)፡፡ "በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መርሃ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች ትንተናና ግምገማ፡፡" በአዲስ አበባ ዮኒቨርስቲ በድህረ ምረቃ መርሃ ግብር የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነ-ዘዴ፣ 2ኛ ዲግሪ ማሟያነት የተዘጋጀ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቀ:: (2009):: *የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር*። ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ፣ ተፈራ ስዩም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ጥላሁን ከበደ፡፡ (2003) ፡፡ ‹‹የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አተገባበር ፍተሻ›› (በሰሜን ወሎ ዞን በተመረጡ 3 የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት) ፡፡

ፍቅሩ ወ/ኪዳን፡፡ (2002)፡፡ "በሶዶ ከተማ በሚገኙ በሁለት የመንግስት እና በሁለት የግል 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ነጸጽራዊ ግምገማ፡፡ "በአዲስ አበባ ዮኒቨርስቲ በድህረ ምረቃ መርሃ ግብር የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነ-ዘዴ፣ 2ኛ ዲግሪ ማሟያነት የተዘጋጀ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

Anderson, A. and Lynch, T. (1988). *Listening*. Oxford: Oxford University Press.

Boyle, J. P. (1984). *Factors Affecting Listening Comprehension*. English Teaching Forum, 38, 1, 34-37.

Brown, G. and Yule, G. (1983). *Teaching the Spoken Language*. Combridge: CUP.

Byrne, D. (1986). *Teaching Oral English*. London: Longman Group U.K. Limited.

Celce-murcia, M. (1991). *Teaching English as a Second Language*.New York: Longman, Inc.

Grant, N. (1987). *Making the Most of Your Text Book.* London: Longman.

Harmer, J. (1991). *The Practice of English Language Teaching.* New York: Longman.

Kral ,T. (1996). *Teacher Development Making the Right Moves.* Washington D.C English Language Programs Division.

Lynch,T.(1983). *Study Listening. Understanding Lectures and Talksin English*.Cambridge: Cambridge University Press.

Rixon, A. (1986). *Developing Listening Skills.* Hong kong: Macmillan.

Underwood, M. (1989). *Teaching Listening*. London Longman.

Ur, P. (1984). *Teaching Listening Comprehension*. Cambridge: Cambridge University Press.

Yagang, F. (1993). *Listening Problems and Solutions*. English Teaching Forum16-19.

# አባሪዎች

## አባሪ ሀ

አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣ የቋናዎች  ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ ፣ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽኁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በክፍል ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት አተገባበር ለመፈተሽ የተዘጋጀ የምልከታ ቅፅ

- ምልከታው የሚደረግበት ትምህርት ቤት ____________________
- ምልከታው የሚደረግበት ምድብ /ክፍል/ ______________________
- ምልከታው የሚደረግበት ቀን ________________________
- ምልከታው የሚደረግበት ሰዓት _________________
- ምልከታው በሚደረግበት ወቅት የነበረው የዕለቱ ትምህርት ርዕስ ______________

ማሳሰቢያ ‹‹እስማማለሁ››፣  ‹‹የለም›› እና ‹‹አልስማማም›› በሚለው ስር ይህን የ‹‹√›› ምልክት በማድረግ መልሱ

| ተ.ቁ | የቀረበው ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | የለም | አልስማማም |
| 1 | የቅድመ ማዳመጥ ክንውን ተግባራት | | | |
| 1.1 | ተማሪዎችን አነቃቅተዋል? | | | |
| 1.2 | ርዕሱን አስተዋውቀዋል? | | | |
| 1.3 | ተማሪዎች ከዚህ በፊት በርዕሱ ዙሪያ የሚያውቁት የቀደመ እውቀት እንዳላቸው በመጠየቅ እውቀታቸውን ገምግመዋል? | | | |
| 1.4 | በርዕሱ ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ሀሳቦች/ነገሮችን እንዲገምቱ አድርገዋል? | | | |
| 1.5 | ከእለቱ ትምህርት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መርጃ መሳሪያዎች በማቅረብ አስተያየት እንዲሰጡ አድርገዋል? | | | |
| 2 | የማዳመጥ ጊዜ ክንውን ተግባራት | | | |
| 2.1 | በማዳመጥ ጊዜ ንባቡን ሲያቀርቡ ቆም እያሉ ቀጥሎ ምን | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ሊሆን እንደሚችል ተማሪዎች እንዲገምቱ ያደርጋሉ? | | | |
| 2.2 | መምህሩ ለተማሪዎች ምንባቡን ያነበቡበት ሁኔታ ማራኪነት አለው? | | | |
| 2.3 | ማዳመጥን ሲያቀርቡ ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲሰሩ በቂ ጊዜ ለመስጠት አንቀፆችን በእርጋታና በድጋሜ ያነባሉ? | | | |
| 2.4 | ተማሪዎች የሚያደምጡት ምንባብ ከራሳቸው የህይወት ልምድ ጋር እንዲያዛምዱ ያደርጋሉ? | | | |
| 3 | የድህረ ማዳመጥ ክንውን ተግባራት | | | |
| 3.1 | ለተማሪዎች ተጨማሪ መልመጃዎችን ይሰጣሉ? | | | |
| 3.2 | ካደመጡት ነገር ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ፅሑፎች እንዲያነቡ ያደርጋሉ? | | | |
| 3.3 | ተማሪዎች ካደመጡት ነገር ውስጥ የተሰማቸውን እንዲናገሩ እና እንዲፅፉ እድል ይሰጣሉ? | | | |
| 3.4 | ተማሪዎች ባደመጡት ነገር ላይ በግል ወይም በቡድን ሆነው እንዲወያዩ ፤ እንዲከራከሩና እንዲሰሩ ያደርጋሉ? | | | |
| 3.5 | ለተማሪዎች መልሶችን በፅሁፍና በቃል ምላሽ ይሰጣሉ? | | | |

# አባሪ ለ

አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ ፣ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በስምንተኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ መጠይቅ

ይህ መጠይቅ በጉራጌ ዞን በመስቃን ወረዳ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርን ለመፈተሽ የተዘጋጀ መረጃ መሰብሰቢያ ነው፡፡ ይህን መረጃ ለመሰብሰብ መምህራን አስፈላጊ ሆነው ስለተገኙ መምህራን ይህን መጠይቅ ለመሙላት ቀና ትብብር ስላደረጉልኝ አመሰግባለሁ፡፡

መጠይቁን ሲሞሉ

1. ስም አይፃፍም
2. በሰንጠረዥ ለቀረበው ጥያቄ " እስማማለሁ" ፣ "የለም" እና " አልስማማም" በሚለው ስር የ ‹‹√›› ምልክት ያስቀምጡ፡፡

- የትምህርት ቤቱ ስም __________________________
- ፆታ_____________
- እድሜ ________________
- የትምህርት ደረጃ ___________________
- የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ _________
- የአገልግሎት ዘመን __________________
- የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ አብይ _________

ንዑስ ___________

**ክፍል ሁለት**

| ተ.ቁ | የቀረበው ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | የለም | አልስማማም |
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ መቅረቡ አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ? | | | |
| 2 | በተማሩባቸው የትምህርት ተቋማት ያገኙት እውቀት ማዳመጥን ለማስተማር በቂ ነው ብለው ያምናሉ? | | | |
| 3 | የማዳመጥ ክሂል በክፍል ውስጥ በራስ ዝግጅት ሲቀርብ ተማሪዎች በንቃት ይከታተላሉ ብለው ያምናሉ? | | | |
| 4 | የማዳመጥ ክሂል ትምህር የክፍል ውስጥ አቀራረብን አስመልክቶ ከመደበኛ ስልጠናዎች በተጨማሪ በልዩ ስልጠና ፣ በንባብ፣ በልምድ ልውውጥ እውቀት ለማግኘት የታደሉበት ጊዜ አለ? | | | |
| 9 | የቅድመ ማዳመጥ ክንውን ተግባራት | | | |
| 9.1 | የዕለቱን የማዳመጥ ትምህርት ርዕስ በቃል በመግለፅና ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ያስተዋውቃሉ? | | | |
| 9.2 | በርዕሱ ዙሪያ ከዚህ በፊት የሚያውቁት ጉዳይ እንዳለ በመጠየቅ የተማሪዎችን የቀድመ እውቀት ይገመግማሉ? | | | |
| 9.3 | በርዕሱ ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ሀሳቦችን እንዲገምቱ እድል ይሰጣሉ? | | | |
| 9.4 | ከእለቱ ትምህርት ጋርተያያዥነት ያላቸው መርጃ መሳሪያዎችን በማቅረብ አስተያየት እንዲሰጡ ያደርጋሉ? | | | |
| 9.5 | የማዳመጥ ይዘቱን ከማንበባቸው በፊት ተማሪዎች ለማዳመጥ ዝግጁ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ? | | | |
| 9.6 | በማዳመጥ ጊዜ የሚሰሯቸውን ጥያቄዎች ቀድመው በመስጠት እንዴት መስራት እንዳለባቸው ማብራሪያ ይሰጣሉ? | | | |

10. የማዳመጥ ጊዜ ክንወን ተግባራት

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | የለም | አልስማማም |
| 10.1 | በማዳመጥ ጊዜ ንባቡን ሲያቀርቡ ቆም እያሉ ቀጥሎ ምን ሊሆን እንደሚችል ተማሪዎች እንዲገምቱ ያደርጋሉ? | | | |
| 10.2 | የማዳመጥ ይዘቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ በቂ ጊዜ ሰጥተው አንቀፆችን በእርጋታና በድጋሚ ያነባሉ? | | | |
| 10.3 | ተማሪዎች ያዳመጡትን ምንባብ ከራሳቸው የህይወት ልምድ ጋር እንዲያዛምዱ ያደርጋሉ? | | | |

11 የድህረ ማዳመጥ ጊዜ ክንውን

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | የለም | አልስማማም |
| 11.1 | ተማሪዎች ካደመጡት ነገር ውስጥ የተሰማቸውን እንዲናገሩና እንዲፅፉ ያደርጋሉ? | | | |
| 11.2 | ተጨማሪ መልመጃዎችን ይሰጣሉ? | | | |
| 11.3 | ካዳመጡት ምንባብ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ፅሑፎች እንዲያነቡ ያደርጋሉ? | | | |
| 11.4 | ባደመጡት ነገር ላይ በግል ወይም በቡድን ሆነው እንዲወያዩ ፤ እንዲከራከሩ እና እንዲሰሩ ያደርጋሉ? | | | |
| 11.5 | ለተማሪዎቹ መልሶችን በፅሑፍ ወይም በቃል ምላሽ ይሰጣሉ? | | | |

**ክፍል ሶስት**

12. የማዳመጥ ትምህርት ክሂል በክፍል ውስጥ ለመተግበር ተፅዕኖ የሚያሳድሩት ነገሮች ምን ምን ናቸው ብለው ያስባሉ?________________________________________

__________________________________________________________

13. መፍትሄዎቹስ? ________________________________________________

__________________________________________________________

# አባሪ ሐ

አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣ የቋንቃዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ ፣ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

ይህ መጠይቅ በጉራጌ ዞን በመስቃን ወረዳ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባሰበርን በመፈተሽ የተዘጋጀ መረጃ መሰብሰቢያ ነው፡፡ ይህን መረጃ ለመሰብሰብ የተማሪዎች ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ ተማሪዎች ይህን መጠይቅ ለመሙላት ቀና ትብብር ስለሚያደርጉልኝ ከወዲሁ አመሰግናለሁ፡፡

መጠይቁ ሲሞላ

1. ስም አይፃፍም
2. በሰንጠረዥ ለቀረቡት ጥያቄዎች "እስማማለሁ" ፣ "የለም" እና" አልስማማም" በሚል ሥር ይህንን የ‹‹√›› ምልክት ያስቀምጡ፡፡

**ክፍል አንድ**

1. የትምህርት ቤቱ ስም____________________________
2. የክፍል ደረጃ ________________________________

**ክፍል ሁለት**

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጭ መልሶች | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እስማማለሁ | የለም | አልስማማም |
| 3 | የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ማቅረቡ አስፈላጊ ነው ብለሽ/ህ ታምኚያለሽ/ታምናለህ? | | | |
| 4 | የቅድመ ማዳመጥ ክንውን | | | |
| 4.1 | መምህራቹ የእለቱን ትምህርት ርዕስ ሰሌዳ ላይ በመፃፍ በቃል በመግለፅ ያስተዋውቋችኃል? | | | |
| 4.2 | በርዕሱ ዙሪያ ከዚህ በፊት የምታውቁት ጉዳይ እንዳለ የቀደመ እውቀታችሁን ተጠቅማችሁ እንድትመልሱ ይጠይቋችኃል? | | | |
| 4.3 | በርዕሱ ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ሀሳቦችን እንድትገምቱ እድል ይሰጧችኃል? | | | |
| 4.4 | ከእለቱ ትምህርት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መርጃ መሣሪያዎችን በማቅረብ አስተያየት እንድትሰጡ ያደርጓችኃል? | | | |
| 4.5 | የማዳመጥ ይዘቱን ከማቅረባቸው በፊት ለማዳመጥ ዝግጁ መሆናችሁን ይጠይቋችኃል? | | | |
| 5 | የማዳመጥ ጊዜ ክንውን | | | |
| 5.1 | መምህራቹሁ በማዳመጥ ጊዜ ንባቡን ሲያቀርቡ ቆም እያሉ ቀጥሎ ምን ሊሆን እንደሚችል እንድትገምቱ እድል ይሰጠጧችኃል? | | | |
| 5.2 | የማዳመጥ ይዘቱን ሲያቀርቡ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ በቂ ጊዜ ሰጥተው አንቀፆችን በእርጋታ እና በድጋሚ ያነቡላችኂል? | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 5.3 | የምታደምጡትን ምንባብ ከራሳችሁ የህይወት ልምድ ጋር እንድታዛምዱ ያደርጓችኃል? | | | |
| 6 | የድህረ ማዳመጥ ክንውን | | | |
| 6.1 | ካደመጣችሁት ነገር ውስጥ የተሰማችሁን እንድትፅፉ እና እንድትናገሩ ያበረታቷችኃል? | | | |
| 6.2 | ተጨማሪ መልመጃዎችን ይሰጧችኃል? | | | |
| 6.3 | ካደመጣችሁት ምንባብ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ፅሑፎችን እንድታነቡ ያዟችኃል? | | | |
| 6.4 | ባዳመጣችሁት ነገር ላይ ተመስርታችሁ በግል. በቡድን ሆናችሁ እንድትሰሩ እንድትወያዩ እና እንድትከራከሩ ያደርጉአችኃል? | | | |
| 6.5 | ለመልሶቻችሁ በቃል ወይም በፅሑፍ እርማት ይሰጧችኃል? | | | |

## ማረጋገጫ

በጉራጌ ዞን በመስቃን ወረዳ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ትንተና (በተመረጡ አራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት); በሚል ርዕስ የተሰራው ይህ ጥናት የራሴ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም አይናለም ጴጥሮስ

ፊርማ --------------------------

ቀን ነሐሴ 2015ዓ/ም